# ማን ነው የአለማት ጌታ?

ብቸኛው ጌታ፣ ፈጣሪ፣ ሰጪ፣ ከሁሉም በላይ የሆነ ተቆጣጣሪ፣ ጥበበኛ፣ አዋቂ፣ ዘላለም ነዋሪ፣ ቀጣይ-ማብቂያ የሌለው፣ ሁሉን ተመልካች፣ ሁሉን አድማጭ፣ በጣሙ መጪቅ፣ በጣሙን ሲቅ፣ ሁሌም ንቁ፣ እጅግ በጣም ሩህሩህ፣ እጅግ በጣም አዛኝ፣ ይቅር ባይ፣ ሃያል፣ አዛዥ፣ ደግ፣ ጠንካሪ፣ ሁሉን ነገርና ሁናቴዎች የሚቆጣጠረው መልካምን በመልከም ለጋሽ፣ ጥራት ልዕልና ሁሌም የርሱ የሆነው አሏህ!

ማን ነው የአለማት ጌታ?

የጀግኖች ሁሉ ጀግና፣ የባለስልጣኖች ሁለ ባለስልጣን የነገስታቶች ሁለ ንጉስ፣ የአዛዦች ሁለ አዛዥ፣ የጠንካሮች ሁለ ጠንካራ፣ የአስተዋዮች ሁለ አስተዋይ የጠቢባን ሁለ ጠቢብ፣ የፈዋሾች ሁለ ፈዋሽ፣ የተመልካቾች ሁለ ተመልካች የሰሚዎች ሁሉ ሰሚ፣ ...የጥበብ ሁለ ባለቤት የሆነው ጥራትና ልዕልና የተገባው አላህ!

ማን ነው የአለማት ጌታ?

በሰማይ በምድር ብለም በሁሉም አለማት ያለት ክብሮች በሙለ ለርሱ የተገቡት በላቀና በልዩ ችሎታው ሁሉን ነገር ሁን ለማለት ማድረግ የሚችል ጥራትና ልዕልና የርሱ የሆነው አላህ!

ማን ነው የአለማት ጌታ?

እንደርሱ ሲመለክ ቅንጣት ታህል እንኳ ዋጋ ያለው አንድም ኃይል የለም...እርሱ አንድዬ ሲቀር፣ በጣም በተዋቡት ስሞቹ የላቀ ግርማን በባህሪነትና በመለዮነት የጐናፀፈው ጥራት ልዕልና የገባው - አላህ!

አላህ ከርሱ ሌላ አምላክ የለም ለርሱ መልካሞች የሆኑ ስሞች አሉት

/ጣሃ/ 20፣ 8

ማን ነው የአለማት ጌታ?

የሚሻውን ያደርጋል፣ የሚሻውን ይፈርዳል፣ ሁሌም ትክክለኛ፣ ሁሌም ፍትሃማ የሆነው ጥራት ልዕልና የተገባው - አላህ!

"ጌታህም የሚሻውን ይፈጥራል፤ ይመርጣልም፤"

/አል ቀሶስ/ 28፣68

ማን ነው የአለማት ጌታ?

ምድር፣ ብለም ሰማያት የርሱው ግዛቶች ናቸው፡፡ የሚሻውን ከፍ ያደርጋል፣ የሚሻውን ዝቅ ያደርጋል፣ ሀይል፣ ጥበብ፣ ብልሃት፣ ምጥቀት ማስተዋል የርሱ የሆነው ጥራት ልዕልና የተገባው - አላህ!

> «/ሙሃመድ ሆይ!/ በል፡- የንግስና ባለቤት የሆንክ አላህ ሆይ... ልምትሻው ሰው ንግስናን ትሰጣለህ፣ ከምትሻው ሰው ንግስናን ትገፋለህ፤ የምትሻውንም ሰው ታልቃለህ፤ የምትሻውን ሰው ታዋርዳለህ፡፡ መልካም ነገር ሁለ በእጅህ /በችሎታህ/ ነው፤ አንተ በነገሩ ሁሉ ላይ ቻይ ነህና!»
>
> /አል ኢምራን/ 3፡26

ማን ነው የአለማት ጌታ?

ህይወትን የሚሰጥ ሞትን የሚያመጣ ነፍስ በጥበብ መዳፉ ያለት፣ እርሱ በፍፁም የማይሞት ዘላለም የሚኖር፣ በሰማያት በምድር ያለው ሁለ ከርሱ የማይደበቅ ጥራት ልዕልና የተገባው - አላህ!

> «አላህ ህያው ያደርጋል፤ ይገድላልም፡፡ አላህም የምትሰሩትንም ሁሉ ተመልካች ነው፡፡»
>
> /አል ኢምራን/ 3፡ 156

ማን ነው የአለማት ጌታ?

ፍጡራን ሁለ በትዕዛዙ የፈጠሩ፣ የክብሮች ክብር የርሱ የሆኑ በክብር ዙፋን ላይ ያለው ጥራት ልዕልና የተገባው - አላህ!

> «ንቁ መፍጠርና ማዘዝ የርሱ ብቻ ነው የአለማት ጌታ አላህ /ክብሩ/ ላቀ፡፡»
>
> /አል አዕራፍ/ 7፡ 54

ማን ነው የአለማት ጌታ?

የመጀመሪያም ነው፣ ከርሱ በፊት ምንም ነገር አልነበረም፤ የመጨረሻም ነው ከርሱ በኋላ ምንም ነገር አይኖርም፣ በጣም የራቀ ነው፣ ከርሱ በላይ የራቀ ምንም የለም፤ በጣም ቅርብ ነው ከርሱ የቀረበ ምንም የለም፤ የነገሮች ሁለ ነገር /ሁናቴ/ አዋቂ የሆነው ጥራትና ልዕልና የተገባው - አላህ!

> «እርሱ ፊትም ያለ፣ ኋላም ቀሪ፣ ግልፅም ስውርም ነው፤ እርሱ ነገሩን ሁለ አዋቂ ነው፡፡»
>
> /አል ሃዲድ/ 57፡ 3

ማን ነው የአለማት ጌታ?

እርሱ የገሮችን ሁሉ ሁለንተናዊ ግኝትና ሁናቴን ሲደርስበት ለማይችለው ጥበቡ የማያውቅ ጥራት ልዕልና የተገባው - አላህ!

«ይኸችሁ ጌታችሁ አላህ ነው፤ ከእርሱ በቀር አምላክ የለም ነገርን ሁሉ ፈጣሪ ነው፡፡ ስለዚህ ተገዙት እርሱም በነገሩ ሁሉ ላይ ተጠባባቂ ነው፡፡»

/አል አንዓም/ 6፡ 102

ማን ነው የአለማት ጌታ?

አይንን ፈጥሮ ብሌንን የሰጠ፣ ግና...አይኖች በጭራሽ የማያዩት እርሱ ፍጥረተ አለሙን ለማየት የሚችል ንቁ አምላክ! ጥራትና ልዕልና የተገባው - አላህ!

«አይኖች አያገኙትም /አያዩትም/ እርሱምአይኖችን ያያል እርሱም - ርህራሄው - ረቂቁ ውስጥ አዋቂው ነው፡፡»

/አል አንዓም/ 6፡ 103

ማን ነው የአለማት ጌታ?

ለሰማይ - በምድር ያሉት ነገሮች ሁሉ ባለቤት የእውቀት አድማሱ ወሰን ድንበር የሌለው ታላቁ አምላክ ጥራትና ልዕልና የተገባው - አላህ!

«በሰማያትና በምድር ያለው ሁሉ የአላህ ነው፡፡ አላህ በነገሩ ሁሉ ለእውቀት ከባቢ ነው፡፡»

/አል ኒሳዕ/ 4፡ 126

ማን ነው የአለማት ጌታ?

ዘላለም ነዋሪ፣ ሳይቋረጥ ቀጣይ ሆኖ ነገሮችን ቀጣይ የሚያደርገው የሰማያት የምድሩ ባለቤት፤ ከእርሱ ምንም ነገር ሲሰውር የማይችለው እርሱ ይቆጣጠር እንጂ እርሱን ማንም የማይቆጣጠረው! ያለፈውን ያሁኑንንም የወደፊቱንም የሚያውቀው ያሰብነውን የምናስበውን የወደፊቱንም የሚያውቀው ያሰብነውን የምናስበውን ለወደፊት የምናስበውንም የሚያውቀው ያለፉት ትውልዶች በሙሉ ምን እንደሰው የሚያውቀው የመልካችንን የፀባያችንን የአሻራችንን መለያየት አብጠርጥሮ የሚያውቀው የሰማይ የምድር ሚዛንን የሚያውቀው የውሃ የውቅያኖስ ጥልቀት መጠንን የሚያውቀው በውሃ ውስጥ ያሉትን እንስሳት አይነት ብዛት ሁናቴ የሚያውቀው...ይህ የላቀው የሰው ልጅ አዕምሮ እርሱነቱን ቢያስበው ከአሳቤው በላይ የሚሆንበት ጥራትና ልዕልና የተገባው - አላህ!

«አላህ ከርሱ በቀር ሌላ አምላክ የለም፤ ህያው ራሱን ቻይ ነው ማንገላጀትም እንቅልፍም አትይዘውም፤ በሰማያት ውስጥና በምድር ውስጥ ያለው ሁሉ የርሱ ብቻ ነው፡፡ ያ እርሱ ዘንድ በፈቃዱ ቢሆን እንጅ የሚያማልድ ማን ነው? /ከፍጡሮች/ በፊታቸው ያለውንና ከኋላቸው ያለውን ሁሉ ያውቃል፡፡ በሻው ነገር እንጂ ከእውቀቱ በምንም ነገር አያካብቡም፤ /አያውቁም/ መንበሩ ሰማያትና ምድርን ሰፋ፤ ጥበቃቸውም አያቅተውም እርሱም የሁሉ በላይ ታላቅ ነው፡፡»

/አል በቀራ/ 2፡ 255

ማን ነው የአለማት ጌታ?

ሁሉን ነገር ያውቃል፤ የሁሉንም ነገር ስሌት የመዘግባል፤ የርሱን ስሌትና ምዝገባ የሂሳብ ጠበብትና ፈላስፋዎች፤ የሰናፍጭ ቅንጣት ታህል እንኳ አይደርሱም ሙታንን ህያው አድራጊ ጥራትና ልዕልና የተገባው - አላህ!

«እኛ በእርግጥ ሙታንን ህያው እናደርጋለን ያስቀደሙትን ስራ ፍላጎታቸውንም እንፅፋለን ነገሩንም ሁሉ ገላጭ መሪ በሆነው መፅሃፍ አጠቃለልነው፡፡»

/ያሲን/ 36፡ 12

ማን ነው የአለማት ጌታ?

የአደባባይን የጓዳን አዋቂ የውስጥንም የውጪንም አዋቂ የግልፅንም የስውርን አዋቂ፣ ምስጢርን ሁሉ አዋቂ የሆነው የርሱን ገፅታ ምስጢር ያደረገው ግልፅ የአለማት አምላክ ጥራት ልዕልና የተገባው - አላህ!

«ንቁ! እነርሱ ከአላህ ይደበቁ ዘንድ ደረቶቻቸውን ያጥፋሉ ንቁ! ልብሶቻቸውን በሚከናነቡ ግዜ የሚደብቁትን - የሚገልፁትን ሁሉ ያውቃል - እርሱ በደረቶች ውስጥ ያለውን ሁሉ አዋቂ ነውና»

/አል ሁድ/ 11፡ 5

ማን ነው የአለማት ጌታ?

እጅግ በጣም ሰጪ ደግ የፀጋ የሲሳይ ባለቤትና ምንጭ የሆነው ጥራትና ልዕልና የተገባው - አሏህ!

«በምድርም ላይ ምንም ተንቀሳቃሽ የለችም፤ ምግቧ በአላህ ላይ ያለ ቢሆን እንጂ፤ ማረፊያዋንም መርጊያዋንም ያውቃል...»

/አል ሁድ/ 11፡ 6

ማን ነው የአለማት ጌታ?

ፀጋው የማይቆጠር ፀጋው የማይታመን ፀጋው የማይለካ የፀጋዎች ሁሉ ባለቤት ጥራትና ልዕልና የተገባው - አሏህ!

«ከለመናችሁትም ሁሉ የሰጣችሁ ነው፡፡ የአላህንም ፀጋ ብትቆጥሩ አትዘልቋት፡፡»

/ኢብራሂም/ 14፡ 34

ማን ነው የአለማት ጌታ?

ምድር ሰማይን ሰሲሳይ በፀጋው የሚሞላው ጥራትና ልዕልና የተገባው - አሏህ!

«የሰማያትና የምድር ድልቦች የአላህ ናቸው»

/አል ሙናፊቁን/ 63፡ 7

ማን ነው የአለማት ጌታ?

ከፍላጎቶች ሁሉ ነፃ የሆነ፣ ለባሮቹ ይሰጥ እንጂ እርሱ በፍፁም የሚይቀበል አድናቆት ውዳሴ የርሱ የሆነው ጥራትና ልዕልና የተገባው - አሏህ!

«እናንተ ሰዎች! እናንተ /ሁል ጊዜ/ ወደ አላህ ከጃዮች ናችሁ አላህም እርሱ ተብቃቂው ምስጉኑ ነው፡፡»

/ፋጢር/ 35፡ 15

ማን ነው የአለማት ጌታ?

በበረከቱ ዝናብን የሰጠ፣ ዝናብን መጥኖ የሚያንሻሻ ምድርን የሚያለመልም አዝመራን የሚሰጥ ጥራትና ልዕልና የተገባው - አሏህ!

«አላህ ከሰማይ ውሃን ማውረዱንና ምድር የምትለመልም መሆኗን አታይምን?»

/አል ሃጅ/ 22፡ 63

ማን ነው የአለማት ጌታ?

መሬትን ለኛ የገራ፣ ባህሩን ለመንጓዣና ለምግብ ለቀማ የገራ ሰማይን ያለምሰሶ የዘረጋ ሩህሩህ አዛኝ የሆነው ጥራትና ልዕልና የተገባው - አሏህ!

«አላህም በምድር ውስጥ ያለን ለናንተ የገራላችሁ መርከቦችም በባህር ውስጥ በፍቃዱ የሚንሻለሉ ሲሆኑ /የገራላችሁ/ መሆኑን፣ ሰማይንም በፍቃዱ ካልሆነ ለምድር ላይ እንዳትወድቅ የሚይዛት መሆኑን አላየህንምን?»

/አል ሃጅ/ 22፡ 65

ማን ነው የአለማት ጌታ?

የሚታየውንም የማይታየውንም አዋቂ፣ የሩቁንም የቅርቡንም አዋቂ፣ ሁሌም ሀያል ሁሌም አሸናፊ የሆነው ጥራትና ልዕልና የተገባው - አሏህ!

«ሩቁን ምስጢር ግልፁንም ሁሉ አዋቂ አሸናፊው ጥበበኛው ነው፡፡»

/አል ተጋቡን/ 64፡ 18

ማን ነው የአለማት ጌታ?

በአሳቢም አንድ የሆነ፣ በተግባርም አንድ የሆነ፣ በተግባርም አንድ የሆነ በአምልኮ አንድ የሆነ፣ በውዳሴ አንድ የሆነ በመንፈስም አንድ የሆነ፣ በቀስ አካል የማይመስል አምሳያ ብጤ የሌለው፣ አጋር የሌለው ዘላለም ነዋሪ የሆነ፣ ክብር ሁሉ የርሱ የሆነው የማይወልደው፣ የማይወለደው ጥራትና ልዕልና የተገባው - አሏህ!

«በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው፡፡»
«በል፡- እርሱ አንድ ነው፡፡ አላህ የሁሉ መጠጊያ ነው አልወለደም አልተወለደም
ለርሱም አንድም ብጤ ለውም፡፡»

/አል ኢኽላስ/ 112፡ 1-4

ማን ነው የአለማት ጌታ?

ክብር ምስጋና ውዳሴ የርሱ የሆነው፣ በባህሪውና በምርጥ ስሞቹ የሚለየው የአምልኮ ፈለግ ለርሱ ወደርሱ ብቻ የሚሆነው ጥራትና ልዕልና የተገባው - አሏህ!

«ስልጣን የርሱ ብቻ ነው ከርሱ ሌላ አምላክ የለም ታዲያ ወዴት ትዞራላችሁ?»

/አል ዙመር/ 39፡ 6

ማን ነው የአለማት ጌታ?

በክብሩ በባህሪው በፈጠራቸው ፍጡራን ሁናቴ ለእውቀት በብቃት በጥራት በተዓምር መለዮው አምልኮ ለርሱ ብቻ የሆነ ጥራትና ልዕልና የተገባው - አሏህ!

> «ጌታችሁ ያ ሰማያትንና ምድርን በስድስት ቀናቶች ውስጥ የፈጠረ አላህ ነው፤ ከዚያም ነገሩን ሁሉ የሚያስተናብር ሲኾን /በአርሹ/ ላይ ስልጣኑ ተደላደለ ከርሱ ፈቃድ በኋላ ቢሆን እንጅ አንድም አማላጅ የለም፤ ይሃችሁ አላህ ጌታችሁ ነውና ተገዙት አትገሰፁምን?»
>
> /ዩኑስ/ 10፡ 3

ማን ነው የአለማት ጌታ?

ሁሉን ነገር ፈጣሪ፣ ሁለን ነገር አስተካከለ፣ ህግን አወጣ መመሪያን ሰጠ፣ የወደፊት ዕቅድን ቸረ፣ ሲሳይ ፀጋ በረከቱን ዘረጋ ጥራትና ልዕልና የተገባው - አሏህ!

> «አላህ ያ ምድርን መርጊያ፣ ሰማይን ጣሪያ ያደረገላችሁ ነው፡፡ የቀረጻችሁም ቅርፃችሁን ያሳመረ ከጣፋጮችም ሲሳዮች የሰጣችሁ ነው፡፡ ይሃችሁ ጌታችሁ አላህ ነው የአለማት ጌታ! አላህ - ላቀ፡፡»
>
> /አል ሙእሚን/ 40፡ 64

አምላካችን ሆይ!

ለዚህ ለታላቅ ክብርህ፣ ለዚህ ለታላቅ ችሎታህ፣ ለዚህ ለታላቅ ብቃትህ ለዚህ ለማያልቅ ፀጋህ ለዚህ ለማያልቅ ሲሳይህ ለዚህ ለማይልቅ በረከትህ ምስጋና ላንተ ብቻ ነው…ያ!…አላህ!

> «ምስጋና በሰማያትም ያለ በምድርም ያለ ሁለ የርሱ ለሆነው አላህ ይገባው በመጨረሻይቱም አለም ምስጋና ለርሱ ብቻ ነው፡፡ እርሱም ብልሃተኛው ውስጥ አዋቂው ነው፡፡»
>
> /ሰበእ/ 34፡ 1

አምላካችን ሆይ!

ለነዚህ የጥበብህ ውጤት ለሆኑት ድንቅ ፍጡራን ከልብ ከመነጨ እውነተኛ ስሜት በአያሴው ልትመሰገን ይገባሃል…ያ!…አላህ!

«ምስጋና ለዚያ ሰማያትንና ምድርን ለፈጠረው ጨለማዎችንና ብርሃንንም ላደረገው አላህ የገባ ነው፡፡»

/አል አንዓም/ 6፡ 1

አምላካችን ሆይ!

ምስጋና ላንተ ነው፣…እስላምን ስለሰጠኸን…ምስጋና ላንተ ነው ቁርኣንን ስላወረድክልን፣ ምስጋና ላንተ ነው ምልካም ፀጋዎች ስለቸርከን፣ ምስጋና ላንተ ነው ምርጥ ትውልዶች ስላደረግከን ምስጋና ላንተ ነው፡፡ በታላቅ ፀጋዎችህ ባርከህ ሰው አድርገህ እንድንከበር ስላደረግከን፣ ምስጋና ላንተ ነው፡፡ ምንም ስላላጕደልክብን ያ.. አላህ! ካንተ በስተቀር ምንም ማንም ጌታ የለም …ያ! አላህ …ክብር ሁሉ ያንተ ነው፡፡ ማዘዝ ሁሉ ያንተ ነው…መታዘዝ ደግሞ የፍጡራን ነው፡፡ ፍጥረታት በሙለ ያንተ ናቸውና!…ያ!…አላህ

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው

ምስጋና ለአላህ ይገባው
የአለማት ጌታ ለሆነው
እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ፣
የፍርዱ ቀን ባለቤት ለሆነው፡፡
አ ን ተ ን ብቻ እንገዛለን፣
አንተን ብቻ እርዳታ እንለምናለን፡፡
ቀጥተኛውን መንገድ ምራን፡፡
የነዚያን በነርሱ ላይ በጐ የዋልክላቸውን
በነርሱ ላይ ያልተቆጣህባቸውንና
ያልተሳሳቱትን ሰዎች መንገድ/ምራን፤ በሉ/

/አል ፋቲሃ/ 1፡ 1-7

አምላካችን ሆይ! ተመስገን ለብስራትህ!

«ዛሬ ሃይማኖታችሁን ለናንተ ሞላሁላችሁ ፀጋዬንም በናንተ ላይ ፈፀምኩ ለናንተም እስልምናን ከሃይማኖት በኩል ወደድኩ፡፡»

/አል ማኢዳህ/ 5፡ 3

_______ ልብ ያለው ልብ ይበል! _______

# <u>የስነ ፍጥረታት ሳይንሳዊ ቅኝት፤ በቁርኣን ሲካተት</u>

መቼም ጆሮ አይሰማው የለ! አይን አያየው የለ! የአላህ /ሱ.ወ/ የተዓምር ግዝፈት፣ የሙያ ብቃቱ ምጥቀት፣ ለየቅል ነው፡፡ ባንፃሩ የቁርኣን ሳይንሳዊ ድምቀት ዘመን የማይሽረውን የህይወትን የፍጡራንን ምስጢራዊ ገፅታ ሰንቆ፣ የው ልጅ ሐቅን ለመቋደስ ሲራብ የመንፈስ ዳቦ ሆኖ - ፍጆታውን ይሞላል፡፡

የዛሬው አምዳችን ታላቁ ፍንዳታ (Big bang) ነው፡፡ የስነ ፈለክ /የከዋክብት ጥናት/ ተመራማሪዎች ሲያብራሩ «ስነ ፍጥረታት (Universe) አንድ ትልቅ አካል ነበር፡፡ ከዚያም ታላቁ ፍንዳታ (Big bang) የተሰኘው ታላቅ የመለያየት ፍንዳታ ተከሰተና Galaxy /የከዋክብት ጥርቅምን አስገኘ፣ ከዚያም ክዋክብት ተገኙ በመቀጠል መሬትን መሳይ ፕላኔቶች፣ ፀሃይ፣ ጨረቃ ወዘተ. ተከሰቱ፡፡» ይህ እውነታ ድንቅና ልዩ በመሆኑ ባጋጣሚ የመከሰቱ ጉዳይ ሳይታለም የተፈታ ነው፡፡ ከላይ የተጠቀሰውን ሳይንሳዊ እውነታ ቁርኣን ጥርት ባለ መልኩ አስቀምጦታል፡፡

እነዚያ የካዱት ሰማያትና ምድርን የተጣበቁ የነበሩና የለያየናቸው መሆናቸውን አያውቁምን?

አል አንቢያ 30

እንግዲህ በዚህ ጭው ባለ የአረቢያ በርሃ፣ የአቧራ ጨለማ በሚጨልምበት ምድር ላይ፣ የአሸዋና የድንጋዩ ሙቀት እንደ እሳት በሚፋጅበት ምድረ በዳ ላይ፣ ድንቁርና ድቅድቅ ያለ ፅልመቱን አንግሶ በነበረበት አረቢያ! ከ1400 ዓመት በፊት ማን ነው ይህንን ሳይንሳዊ ሐቅ ተመራምሮ ለመጪው ትውልድ ያበረከተው?

«እኮ ማን ነው?» የትኛው ቤተ ምርምር (Laboratory) ነው ያጠናው? የትኛው ሞክሮ (Experiment) ነው ያረጋገጠው? የትኞቹ ዶክተሮች፣ ፕሮፌሰሮች፣ ሳይንቲስቶች ናቸው ያፀደቁት?...እውነት እንደ ማለዳ ፀሀይ ፍንትው ብላለች ሁሉም ከግላዊ ግትርነት በመራቅ እራሱን ሲጠይቅ ይችላል! ምላሹም የኪሊማንጃሮ ተራራን ቧጦ የመውጣት ያህልን አያዳግትም ቀላል ነው፡፡ ልብ ያለው ልብ ካለ!

ይህ ነው አለማዊና መንፈሳዊ እሴትን ያጣቀሰ፣ በምርምር፣ በጥትና፣ በምክናታዊነት፣ በዘላለማዊ የእምነት ትጋት የተገነባ መሰረት - ኢስላም! ቁርኣን ከውስጡ በሚፈነጠቅ ብርሃን ደምቆ ወጋግኑ በምድር ዙሪያ በርቷል፡፡ ከአፅናፍ እስከ አፅናፍ ዘልቋል ዳሩ የደረትን የጉድን ሾንቶች አልፎ ከልቦና ላይ በእጅጉ ሰርጎ አለመግባቱ ለምን ይሁን? ልብ ያለው ልብ ይበል!

«ልብ የምታደርጉ እንደሆን ለናንተ ማብራሪያን ገለፅን»

አል ኢምራን 119

ወደ ፍሬ ሃሳባችን እንመለስና ሳይንስ እንዳመላከተው ከሆነ ስነፍጥረታት ወደ ቁስ አካልነት (matter) የተቀየሩት ከታላቁ ፍንዳታ (Big bang) በኋላ ነው። ከዚያ በፊት ሀይል ወይም ጊዜ አልነበረም ይህም የዘመናዊ Physics እውነታን በቁርአን ጥላ ስር አመላክተናል።

በ1992 የNANA ሳተላይ ባነፈነፈው ማስረጃ መሰረት የታላቁ ፍንዳታ (Big bang) ቅሬቶችን በመመርኮዝ ስነ ፍጥረታት ከምንም መፈጠራቸውን አመልክቷል እንግዲህ ይህ «ሁን» ወደሚለው የአላህ /ሱ.ወ/ ትዕዛዝ ያመራናል። ያም የአላህ የማዘዝ ጥበብ ምድር ሰማያትን በውስጣቸው ያዘሉትን አስገኘ።

«እርሱ ሰማያትና ምድርን ያስበጤ ፈጣሪ ነው።»

አል አንዓም 101

የቁስ አካል ወይም ነገር (Matter) ሁናቴን ካነሳን ቃለ በቁርኦን የተጠቀሰ ነው ዳሩ የምርምሮች ሁሉ ወደ አቅጣጫ ቁስ አካል ወይም ነገር (Matter) ከተዘነበለ ይህንንስ ነገር ወይም ቁስ አካል ማን ነው የፈጠ ረው? በርግጥም ያ የማይሞው የማይወልደው የማይወለደው ዘላለም ነዋሪ የሆነው አላህ ነው ጥራትና ልዕልና የተገባው የነገሮች ሁሉ ፈጣሪ። ነው!

«ነገርንም ሁሉ ፈጠረ እርሱም ነገሩን ሁሉ አዋቂ ነው።»

አል አንዓም 101

በአያሌ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ሆጫጭ ያሉ ክዋክብቶችን አይኖ የቻለውን ያህል ይመልከቱ፣ የጨረቃን ድምቀት ይገምቱ፣ የመሬትን ሁናቴ ያስተውሉ እውነትን ያያሉ እውነትና ንጋት አድረው ደጠራሉ - በቸር እንሰንብት! አላህ የተሻለን ያውቃል።

## ከምትወዳቸው አድርገን!

«ፍቅር» የቃሉ ንረትና ግዝፈት ባስንበት አኼሩ ዘማን ከአፅናፍ አፅናፍ እየተመመ ነው። ፍቅርን አስመልክቶ የደራሲያን ብዕር በእጅጉ ይከትባል። የሰዓሊያንም ብሩሽ ሰርክ ይከሽናል። እነሆ! ቃሉ በብዙ ቢሊዮን የሚቆጠር ንዋይ ስማንሸራሸር ታላቅ የኢኮኖሚ አውታር ሆኗል።

ፍቅር የባንኮችን ገንዘብ - ወፈር! የንግድን ሁናቴ ቀየር - ቀየርየር! ተዋንያንን ከትቢያ ላይ አንስቶ ሚሊየነር! የቲቪ፣ የጋዜጣ፣ የሬድዮ፣ የፊልምና የመፃህፍት ዘገባና ትዕይንቶችን ወፈር እያደረገ ነው። በሼክስፒር ብዕር በስፋት የተሎከሰው የፍቅር ነበልባል ከሆሊውድ መሽጐ እስላማዊ አገሮችንም ሳይቀር እማሴውን አናኝቷል። የቢዝነሱ! ፍቅር!

ያፈቀረ ልቦና የተጨነቀ ህሊና የፍቅርን ሙሉ አድራሻ ቢጠየቅ የሚዘነጋው አይመስልም። ግና ይህ እፁብ ድንቅ ቃል የመጠቅለል ባህሪውን ሰንቆ የበርካታ የሐይማኖት ተቋማት መለዮ ሆኖ መገኘቱ እሰየው የሚስብል ነው። ስለምን ቢሉ ሐይማኖት ከገሃዱ አለም ውጪ የሚገኝ ክህሎትን የተጐናፀፈ አምላክ በመሻት የሚደረግ ስነ ልቦናዊና አካላዊ የፍቅር ጉዞ ነውና - ሐይማኖት!

ታዲያ እውነት የጠራ ሆኖ ሳለ በምክንያታዊነት፣ በማመን፣ በማሣመን መጠይቅን እንደ መቅሰፍት የማይቅጥረው ኢስላም የፍቅር ዝናብ እንዳልነካው በተለያዩ የአለም የመገናኛ ብዙሃን ሲተች፣ ሲኮነንና ሲዘለፍ መስማቱ ፍቅርን ፍቅርቅር ያሰኘዋል።

'ፍቅር' ቃሉ በአረብኛ 'ሁብ' ሲሆን በእንግሊዝኛ 'Love' ተብሎ ይጠራል። እንግሊዝኛን ወደ አማርኛ በሚተረጉሙ መዝገበ ቃላት 'Love' ስሚለው ቃል የመጀመሪያ ትርጓሜ በአብዛኛው 'መውደድ' ሲሆን ቀጥሎ ሲቀመጥ የሚያስተዋለው 'ፍቅር' ነው። የኢትዮጵያ ሙስሊም ሊቃውንት /ዑለማ/ ብዙውን ጊዜ ሲጠ ቀሙ የሚስተዋለው መውደድ የሚለውን ቃል በኢስላም የፍቅርን ሰንደቅ ያውለበለበ ስሚመስላቸው ወገኖች ምላሽ ያለን ይመስለናል። የእንግሊዝኛን ኢስላማዊ ሰበካ /ትምህርት/ ስሚከታተል 'Love' የሚለውን ቃል ያለመተኪያ መስማቱ የሚስተዋል ነው።

በዛሬው ዓምዳችን 'የአላህ ፍቅር' በማለት ፈንታ 'የአላህ መውደድ' ማለትን እንመርጣለን ለለምን ቢሉ በዘልማዳዊ ክንውን ወይም በባህላዊ ትግባሬያችን 'እወድሃለሁ እወድሻለሁ' የሚለውን የአነጋገር ዘይቤ ለዘመናት ብሎም አሁንም እየተጠቀምነው ነውና! በአንፃሩ የዘመኑ ፍቅር ለሠላም ለመፅሃፍ ሽያጭ ስምረት አጣፋጭ ቅመም በመሆኑ ፍቅርቅር ሆኗልና!

ታዲያ! እንዴት አላህ /ሰ.ወ/ እንደወደደን ማወቅ እንችላለን?

አላህ ሆይ ከምትወዳቸው አድርገን! ...አሚን!

የአሏህ ውዴታ ምንድን ነው?...እርሱማ ስመልካም ቅድስና የሚደረግ ትግል ነው! የአላህ ውዴታ የልብ፣ የነፍስ ቀለብ፣ ስመንታ አይኖች የደስታ ምንጭ፣ ሙታን የተከለከሉት ህይወት፣ በድቅድቅ ጨለማ ውስጥ ያስብርሃን በህመም ወቅት የማይገኝ ድንቅ ፈውስ፣ በሐሳብ በጭንቀት ደስታን ሳጣ ደስታን የሚቸር ነው የአላህ ውዴታ!

ታዲያ የአላህን ውዴታ እንድንጐናፀፈ የሚያደርጉትን ተግባራት ምንድን ናቸው ከትንታኔው በፊት አንድ የቁርኣን አያን ለአብነት እነሆ!

«በላቸው አላህን የምትወዱ እንደሆናችሁ ተከተሉኝ፤
አላህ ይወዳችኋልና፣ ኃጢዓቶቻችሁንም ለናንተ ይመራልና አላህም መሃሪ አዛኝ ነው፡፡»
አል ኢምራን 31

የረሱልን የአኗኗር ዘይቤ መከተል
ለአማኒያን ትሁት መሆን፤ ከሃዲያን ላይ ማየል፣ ለአላህ ብሎ መታገል፣ አላህን እንጂ ማንንም ምንንም አስመፍራት ይህንንም ባህሪ አላህ /ሱ.ወ/ በፅኑ ሲያመላክተን እንዲህ ብሏል፡፡

«እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ከናንተ ውስጥ ከሐይማኖቱ የሚመለስ ሰውን አላህ /በነርሱ ስፍራ/ የሚወዳቸውንና የሚወዱትን በምእምናን ላይ ትሁቶች በከሃዲዎች ላይ ሐያላን የኾኑትን በአላህ መንገድ የሚታገሉትን የወቃሽን ወቀሳ የማይፈሩንት ህዝቦች በእርግጥ ያመጣል፡፡»
አል ማኢዳህ 54

ከላይ በተዘገበው ቁርኣናዊ አንቀፅ አላህ የሚወዳቸውን ሰዎች መለዮና እጣ ፈንታ ገልጿል፡፡ በከሃዲያን ፊትም ቆራጥ መሆን በፊታቸው ምእምናንን አስማራከስ - አስማዋረድ ተገቢ ነው፡፡ አላህን የወደዱ ለአላህ ብለው ፀረ ሸይጧን፣ ፀረ ከሃዲያን፣ ፀረ መናፍቃን፣ ፀረ ከንኮለኛ አቋም ይኖራቸዋል፡፡ ከራሳቸው ነፍስ ጋርም ታላቅ ተጋድሎ ያረጋሉ፡፡ በተጨማሪም አላህ የወደዳቸው የወቃሾችን - ወቀሳ፣ የአሳባቢዎችን - ሰበብ፣ የአመካኞችን - ምክንያት፣ የነቃፊዎችን - ነቀፋ በፍፁም አይፈሩም፡፡ ስስምን ቢባል ሐይማኖታቸውን ተግባራዊ ያደርጋሉና ነው፡፡

ከምናደርጋቸው የፈርድ ኢባዳዎች ባሻገር የማንገደድባቸውን ኢባዳዎች ለምሳሌ ቅያምን ለአላህ ብለን ስንፈፅም የአላህን ውዴታ ይስግሰናል፡፡ ይህንን የሚያበስረው ሃዲሰል ቁድስ እንዲህ ይነበባል «ባርያዩ በማይገደድባቸው ኢባዳዎች /ፀሎቶች/ ወደኔ ያመራል እኔ እስክወደው ድረስ!»

እርስ በርስ መጠያየቅ /በቁሳዊ ፍላጐት/ መረዳዳት፣ ለአሏህ ብሎ ቀና ምክርን መምከር፡፡ በአህመድ በተዘገበው ሰሒህ ሐዲስ የአላህን የውዴታ ቃል-ኪዳን ረሱል /ሰ.ዓ.ወ/ እንዲህ ብለውት ነበር የአላህን መልእክት

«ለኔ ብለው ለሚዋደዱ /ሁለት/ ሰዎች ለውዴታም ዋስትና አለኝ»

«ለኔ ብለው በቁሣዊ ፍላጐቶች ለሚረዳዱ /ሁለት/ ሰዎች ለውዴታዬ ዋስትና አለኝ»

«ለኔ ብለው ቀረቤታቸውን ለሚያጣብቁ /ሁለት/ ሰዎች ለውዴታዬ ዋስትና አለኝ»

ስለዚህ የአላህን የውዴታ ዋስትና ለመጨበጥ አስላማዊ መዋደድን፣ መረዳዳትን፣ ቀረቤታን የትም ይሁን መቼ እናጠንክር፡፡

ሌላው የአላህ ውዴታ በኛ ላይ እንደሰፈነ አንፀባራቂ ከሆኑት ባህሪያት አንዱ በዱንያ ላይ መፈተን ወይም መሞከር ነው፡፡ ለምሳሌ በአደጋ፣ በሐዘን በበሽታ በኪሳራ ወዘተ፡፡ ለምንወደው ሰው ከበሽታው ይፈወስ ዘንድ መራራ መድኃኒት እንደምንሰጠው ሁሉ በዱንያ የሚገጥመን ፈተና አላህ ለኛ ለፈውስ የሚሰጠን መድኃኒት ነው፡፡

ቲርሚዝና ኢብንማጀህ በዘገቡት ሰሒህ ሀዲስ እንደተነገረው «ታላቅ ምንዳ /አጅር/ ከታላቅ ፈተና ይገኛል፡፡ አላህ ሰዎችን ሲወድ ይሞክራቸዋል ይህንን የተቀበለ የአላህን ደስታ ይጐናፀፋል ቅሬታውን የሚያሰማ ቁጣውን ያገኛል፡፡»

በሙእሚን ላይ የሚደርሱ ፈተናዎች ለአኼራ ከሚቀመጡ ቅጣቶች ይሻላሉ፡፡ ነብዩ /ሰ.ዓ.ወ/ ይህንን አስመልክተው ሲናገሩ አላህ ለባሪያው መልካምን ሲሻ ቅጣቱን በዚህ አለም ላይ ያቀርብለታል፡፡ ለባሪያው መልካምን ሳይሻ ሲቀር ቅጣቱን ለፍርዱ ቀን ያቆየዋል፡፡ በቲርሚዚ የተዘገበ ሰሒህ ሀዲስ ነው፡፡

«አላህ ሆይ ከምትወዳቸው አድርገን!»

*    *    *

ሰውየውን አላህ ሲወደው! ምልክቱ ምንድን ነው?

አዎ! ሰዎች ይወዱታል በምድርም ተቀባይነት ያገኛል፡፡ ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ «አላህ ባሪያውን ሲወድ! ...እካሌን እወደዋለሁ ብሎ ለጂብሪል ይነግረዋል፡፡ ጂብሪልም ያንን ሰው ይወደዋል!... ከዚያም የሰማይን ህዝቦች ይጣራል፡፡ አላህ እካሌን ስለወደደው ውደዱት እያለ» ይህም የዚህን ባሪያ በምድር ያለውን ተቀባይነት ያፀድቀዋል፡፡

በሌላ ሐዲስ አቡሁረይራ /ረ.ዓ/ በአላህ የተወደዱ ሰዎችን ፀጋ በምስራችነት ተናግረውታል፡፡ አላህም እንዲህ አለ «ለኔ ብሎ መስዋዕትነት ለሚከፍል ሰው /ለኔ ሳደረሰው/ ጠላትነት የገጠመ እኔ ከርሱ ጋር ጦርነትን እምራለሁ፡፡ የኔ አገልጋይ ወደኔ በምንም አይቀርበኝም እኔ በርሱ ከምደሰትበት ሐይማኖታዊ ተግባራት እንጂ! በኔ ዘንድ በጣም ይወደዳል፡፡ አሁንም ይህ አገልጋዬ ወደኔ በማይገደድባቸው አምልኮዎች መቅረቡን ይቀጥላል - እኔ እወደው ዘንድ! እኔ ስወደውም... የሚሰማበት መስሚያው ነኝ! የሚያይበት አይኑ ነኝ! የሚዳስስበት እጁ ነኝ! የሚራመድበት እግሩ ነኝ! ... በሚጠይቀኝ ሰዓት እሰጠዋለሁ ጥገኝነትንም ሲሻ ጥገኝነትን አፀድቅለታለሁ ቡኻሪ ዘግበውታል፡፡

የዚህንም ምርጥ ሀዲስ ትርጓሜ የሙስሊም ሊቃውንት እንደሚከተለው አስቀምጠውታል፡፡

ሀ/ የሚሰማበት መስሚያው ነኝ:-

- ባሪያው አላህ ከሚወደው ሌላ ምንም አይሰማም

ለ/ የሚያይበት አይኑ ነኝ:-

- ባሪያው አላህ የሚወደውን እንጂ ሌላ አያይም

ሐ/ የሚነካበት እጁ ነኝ:-

- ባርያው አላህ የሚወደውን እንጂ ሌላን አይነካም

መ/ የሚራመድበት እግሩ ነኝ:-

- ባርያው አላህ ወደሚወደው እንጂ ወደ ሌላ አይጋዝም

ሠ/ ሲጠይቀኝ ሰጠዋለሁ:-

- የባሪያው ዱዓ ተቀባይነት አለው /መቅቡል ነው/

ረ/ ጥገኝነትን ሲሻ ጥገኝነትን አፀድቅለታለሁ:-

- ባርያው ከማንኛውም ክፉ ነገር በአላህ ይጠበቃል

* * *

## አላህ ሆይ ከምትወዳቸው አድርገን! አሚን!

* * *

አላህ ይውደዳችሁ!

# <u>የሐበሻ ቀጠሮ፤ ወይስ የምናፍቅ አሮሮ</u>

የቀጠሮ ጉዳይ ህብረተሰባችንን የሚያብሰለስል፣ የጊዜ ስሌት ሚዛናዊ በሆነ መልኩ እንዳይከናወን የሚያስተጓጉል፣ አንዱን ካንዱ የሚያናቁር፣ እርስ በርስ የሚያቃቅር፣ ከውጪ ሰው ጋር ስንገጥም የሚያሳፍር ተግባራችን መሆኑ የአደባባይ ምስጢር ነው፡፡

ኢስላማዊ ተሞክሮ በአያሌው በግዜ ላይ የተመረኮዘ ነው፡፡ ሰላት በግዜ ስሌት ነው የሚከናወነው፣ ጾም በወርሃ ሮመዳን በተለያዩ ወቅቶች ነው የሚጾመው፣ ባጠቃላይ ምዕምናንን ሁለንተናዊ ተግባራቸውን የሚያበጁት፣ የስኬት መሰረታቸውን የሚገነቡት፣ የቀጠሮውን ህይወት በማሰብ ነውና... የቀጠሮው ህይወት ምንዳን ነው ካለ ሞት ቀጠሮ ነው፣ መቀበር ቀጠሮ ነው፣ የመቃብር ጥያቄ ቀጠሮ ነው፣ በእለተ ትንሳኤ መቀስቀሱ ቀጠሮ ነው፣ ሒሳብ ቀጠሮ ነው፣ ገነት ቀጠሮ ነው፣ ገሃነምም ቀጠሮ ነው

የቀጠሮ እውነታ በኢስላማዊ መርህ ውስጥ ታላቅ ቦታ ያለው ስመሆኑ አሌ አይባልም፡፡ ቀጠሮን የሚያከብር የጊዜን ምንነት አውቆ የዘነጋ ስለሚያስመስል ከእምነት ምህዋር ሳለማፈንገጥ እመርታዊ ለውጥ በማድረግ እራስን ማሻሻሉ የሚያፀድቅ ተግባር ነው፡፡

አላህ /ሱ.ወ/ ለስ ግዜ ታላቅ ዋጋ መሰጠቱን ሲያመላክት በተለያዩ የቁርኣን አናቅጾች ሲምልባቸው መነበቡ ወይም መሰማቱ ግልፅ ነው በዋቢነት ጥቂቶቹን እነሆ:-

በንጋቱም በብርሃን በተተነፈሰ ጊዜ እምላለሁ፡፡

አል ተክዊር 18

በሰማዩ በሌሊት መጪውም እምላለሁ፡፡

አል ጣሪቅ 1

በጐህ እምላለሁ፡፡

አል ፈጅር 1 /የጐህ ምዕራፍ/

በሌሊቱ እምላለሁ /በጨለማው/ በሚሸፍን ጊዜ

ሱረቱል ለይል 1

በረፋዱ እምላለሁ፡፡

አል ዱሃ 1

በጊዜያቱ እምላለሁ፡፡

አል አስር 1

አል አስር የአማርኛ ትርጉም የጊዜ ምዕራፍ ሲሆን የዚህን ምዕራፍ ይዘት ለየት የሚያደርገው፤ በሙስሊም ሙህራን ሌላ የቁርኣን አናቅፅ ባይወርድ ኖሮ ለሰው ልጆች መመሪያነት ይበቃ ነበር መባሉ ነው፡፡ እንግዲህ ልብ ያለው ልብ ይበል በዚህ መሃላ ታላቅ ቁም ነገር አለ ቁርኣናዊ ዋቢን እነሆ

«በዚህ መሃሳ ስባስ አዕምሮ ታሳቅ መሃሳ አስበትን»

አል ፈጅር 5

ታዲያ ስ6 ሰዓት የተጠራ ሰርግ በ9 ሰዓት ከተጀመረ በዙሁር የቀጣጠሩ በአስር ከተገናኙ ስዑማው ምን ይሻስዋል

የሐበሻ ቀጠሮ ብሎ ምክንያት መስጠት አሳህ ይሁነን

ቀጠሮ ስስመዘንጋት፣ የትንታኔ እውነት

1. ኢሞራሳዊ ተግባርን በማጉልበት ግብረገባዊነትን የምፀት ማድረግ ጉጂ ባህልን ማዳበር፣…አስሳም ደግሞ የመልካም ባህል አፀድ በመሆኑ ይህ ከኢስሳም ጋር ይፃረራል
2. የሌሎችን የጊዜ ስሌት ስማወክ ካንዱ ወደ አንዱ የሚያሽከረክር ውስጣዊ ቁርሾን በመጫር፣ የወንድም እህትማማች ውልን በማናጋት አንድነትን ማሳሳት ኢስሳም ደግሞ የአንድነት ቤዛ የአንድነት ሐይማኖት በመሆኑ፣ ይህ ከኢስሳም ያፃርራል፡፡
3. የራስን አድሎአዊ መብት በማፅደቅ የሌሎችን መንጠቅ፣ እኛ ማርፈድ ካልወደድን ሌሎች ስስማይወዱት ነብያዊ ፈስግ ደግሞ ስራስህ የምትወደውን ስወንድምህ መውደድ በመሆኑ ከነብያዊ ፈስግ ማፈንገጥን ያመጣል ይህ ደግሞ ከኢስሳም ያፃርራል
4. ከመጠን ያስፈ መጠባበቅ የአምራችነትን ባህሪን ስስሚቀንስ የህብረተሰበን እድገት ይጉዳል ጠንክሮ መስራት አስሳማዊ መርህ ስስሆነ ይህ ስንፍና ከኢስሳም ያፃርራል
5. ሙስሊም በዘገቡት ሀዲስ ቃል አባይነት ከምናፍቃን ባህሪያት አንዱ በመሆኑ፣ መናፍቆች ከአስሳም ፅንሰ ሃሣብ ይፃረራሉ
6. ቀጠሮ አስማክበር ስውሸት ይዳርጋል፡፡ ውሸት የምናፍቅ ባህሪ ከመሆኑ ባሻገር በነብያዊ ምሪት ቅንጣት ታህል እንኳ መዋሸቱ የተከለከለ ሆኖ አያስ የቁርኣን አናቅፅ በማስጠንቀቂያነት ወርደዋል ይህም ከኢስሳም ያፃርራል፡፡

ብዙ የቀጠሮ አስማክበርን አስከፊ ገፅታዎች ማስረጃ በማጣቀስ ማመሳከት ይችሳል ዳሩ ግን አምድ ስስሚያጠብ ስመፍትሔ ኢሳማነት ያዘጋጀናቸውን ቁም ነገሮች አንኳር አንኳራቸውን ስአብነት የህል እነሆ

ስአበሻ ቀጠሮ፣ የመፍትሔ ተሞክሮ

1. ከሳይ የተጠቀሰውን ቁርኣናዊ ዘገባ ከልብ ከመነጨ እውነተኛ ስሜት በመረዳት እራስን ስስውጥ ማዘጋጀት ስውጥን ዛሬውኑ በቆራጥነት መጀመር፡፡
2. የኑሮ ሁናቴ መካከለኛ ማድረግ ስምሳሌ በመልበስ በመጋጊያጥ የምናረፍድ ከሆነ ውስጣችን በእዩልኝ ስሙልኝ አስመታፈኑን ልብ ማስት ከዚያም ኢስሳማዊ ፅንሰ ሃሣብ ነፅህናን /ጠሃራን/ የሚያዝ

መሆኑን በሚዛናዊነት ከራሳችን ጋር ማዋሃድ ባንፃሩ የመዘነጥ ጥሩት ከማርፈድ መጥሮነት ያነሰ ነው፡፡

3. በቀጠሮአችን ዕለት ይሁን መቼ ግዜን የሚያጠፉ ለህይወታችን አስፈሳጊ ያልሆኑ ነገሮችን ማስወገድ ይህም ትርፍ ጊዜን እንድናገኝ ይህ ነው የማይባል ጠቀሜታ አለው
4. ችግራችን የመርሣት የመዘናጋት ከሆነ እራሳችንን ንቁ ማድረግ

   ሀ/ የማስታወሻ ደብተር መያዝ

   ለ/ /መጥሪያ/ መጠቀም፤ የዘመኑ የእጅ ስልኮች የማስታወሻ መመዝገቢያ፣ የጊዜ ጠቋሚ ደወል ስሳሳቸው መጠቀም ወይም ግልጋሎታቸውን መማር፡፡

   ሐ/ ድምፅን በመቅረፅ ለማስታወሻነት የሚሆኑ መሳሪያዎች ስሳስ መጠቀም ወይም መረጃ ማሰባሰብ
5. የመንገዶቹን ሁናቴ፣ የአየሩን ፀባይ በቲቪ በሬድዮ በጋዜጣ  መኪና እየነዳን እንኳ መከታተል የሚፈጠር ወይም የተፈጠረ አጋጣሚ ካስ ደውስ ማሳወቅ፡፡
6. በማንችለው ስለማንገደድ የማንችል ከሆነ አለመቻሳችንን በስል በ ኤሜይ፣ በደብዳቤ ወይም በመልዕክተኛ ወዘተ ማሳወቅ
7. ስለ ቀጠሮ ማክበር አስፈሳጊነት በቂ ግንዛቤ ለማግኘት እውቀት መቅሰም ለምሳስ ማንበብ፣ ማዳመጥ፣ መወያየት ስዑስሞች ጥያቄ ማቅረብ ወዘተ

ይህ የሐበሻ ቀጠሮ የሚለው የማስተባበያ ፈሊጥ የህብረተሰባችንን መንፈሳዊና አለማዊ ህይወት የሚያናጋ የስነ ልቦና ችግር በመሆኑ በጋራ ሪእንነሳበት የሐበሻ ብቻ ስሆን አይችልም ልብ ያስው ልብ ይበል አሳዓ ከምናፍቅነት ይጠብቀን የምንፅፈውን የምንተገብር ያርገን አሳህ የተሻለን ያውቃል ሃጢአታችንን ይማርልን... አሚን

# ወደ እዩብ ትዕግስት ስማምራት

ትዕግሥት ከሙዳይ አልፎ ከዝንበከልክል ሙሉ ወርቅ ትበልጣለች ቢባል ማጋነን አይሆንም መኖር በዚህች ምድር መሞት፣ መቀበሩ ብሎም ስፍርድ መቀስቀሱ በትዕግስት ጥላ ስር ያለ ሒደት ነውና!

ትዕግስት ፅናታዊ እምነትን በአንድ አምላክ ላይ መጣል ማለት ነው። ባንፃሩ ዘለቄታዊ ታጋሽነት የአንድ መልዓክ ክንዋኔው በሚተገብራቸው የትየለሴ ንጢዓት፤ በጥፋት ትንታግ በተወገደ ነበር፤ ግና ይህ ማኅዕ ፈጣሪ ታጋሽ ነው። በተጨማሪም ምድር በንጢዓት ስትደለቅ በተናደች ነበር ሁሌም ከታጋሾች ጉን የሚሆነው አላህ /ሱ.ወ/ ቻይ አደረጋት።

ትዕግስትን /ሰብር/ ያላካተተ ኢስላማዊ ህይወት የለም ሰብር/ትዕግስት/ ኢስላማዊ ፍኖት ነውና ምዕምናኑም በዚህ የሰናይ ፍኖት ይንዛሉ። በቃላት ሲገለፅ፣ በብዕር ሲከተብ፣ በስዕል ሲሳል የማይችል ውስጣዊ ሰላምን ይጐናፀፋሉ ግና ይህ ውስጣዊ ሰላም ከአልማዝ በላይ ውድ የሆነ ከብረት የጠነከረ የመንፈስ ጋሻ ነውና ...ትዕግስት አልሰብር

የሰው ልጅ የመኖር ሂደት በወደር የለሽ ስስት ተናግቶ ሰብዓዊነት በአብሪት ሾተል እየተገረደፈ፣ አዕምሮ የማይገምተው ለአይን የሚሰቀጥጥ ሁለንተናን በድንጋጤ የሚያርድ የሰብዓዊ መብት መደፈር ዛሬም ይሁን ለዘመናት ተስተውሏል። ከሰው ልጆች በሰው ልጆች የሚፈፀም፤ ታዲያ ከትዕግስት በስተቀር ለታወከ ህሊና ፍቱን መድኃኒት አልነበረውም...የለምውምም።

ትዕግስት ፍላጐት ሲሟላ፣ የሰራ አካል ሲደሰት ሲፈነድቅ እራስን በራስ መቆጣጠሪያ የአላህን ወሰን የማይታለፍበት ኑሮ በኢማን የሚከለልበት የህሊና መረብ ነው።

- ትዕግስት እንደ ኮሶ የመረረ ስፈውስ የምንጐነጨው መራራ መድኃኒት ነው።
- ትዕግስት ዙሪያ ገባው ስጥመት ሲነዘንዝ፣ በዱንያ ሲያማልል ሲታገል፣ ፍትህ አልባነት ኢአማኒነት በሜንጦው ሲያንጠለጥል ሲያደባ መከታነትን የሚችር የፅናት ጋሻ ነው።
- ትዕግስት ሐዘን፣ አደጋ፣ ህመም፣ መታሰር፣ መታረዝ፣ መሰደድ፣ ስራ መፍታት፣ መክሰር፣ ጤና ሲታወክ፣ አካለ ስንኩል ሲኮን፣ ሞት ሲመጣ ወዘተ... ወደላይ የምናሻቅብበት አድካሚ ደረጃ ነው።
- ትዕግስት ምንዳን የሚለግስ፣ ምህረትን የሚያዘንብ ከፈጣሪ የተነገረ የቃል ኪዳን ብስራት ነው። ትዕግስት

> «ግን እነዚያ ታገሱ፤ መልካም ስራዎችንም የሰሩ እነዚያ ለነሱ ምህረትን ታላቅ ምንዳ አላቸው።»
>
> ሁድ 11

«ታዲያ እንዴት ይታገሳሉ
...እንዴትስ ለምህረት ይታጫሉ በምንዳስ ይንበሸበሻሉ እንግዲህ ልብ ካሎት ልብ ይበሉ
የአሳህንም ቃል ያስተውሉ
መልካምን ትዕግስት ታገስ።»

አል መዓሪጅ 5

1. ያልታሰበ አደጋ ሐዘን ሲገጥም ወዲያውኑ መታገስ
    - ኢና ሊላሒ ወኢና ኢለይሒ ራጂዑን ማለት

በዚሁ በአኺሩ ዘማን ከእዮብ የትዕግስት ምንጭ ስመጉንጨት ፅዋዎችንን እንጨብጥና በፀሎት ታንፀን ስጋ መንፈሳችንን በማይወልደው በማይወለደው በማይሞተው ዘላለም በሚኖረው ህያው አንድ አምላክ ህግጋት አናንፃው ለሁለቱም ዓለማት ስኬት ብሩህ ተስፋ ይገኛል።

«እናንተ ያመናችሁ ሆይ! በመታገስና በሰላት ተረዱ፤ አላህ /በእርዳታው/ ከታጋሾች ጋር ነውና።!»

አልበቀራህ 151

ትዕግስት ሁለንተናን የሰራ አካልን ለአላህ አሳልፎ የሚሰጥበት የመስዋዕትነት ጉዞ ነው። ይህ ጉዞ ፅናታዊና መለኮታዊ መከታን በጋሻነት ይችራል። ታጋሹ የትም ይሁን መቼ በጌታው ይመካል በራስ መተማመኑ ይጨምራል። ልቦናው ከጌታው በሚያገኘው የታጋሽነት ምንዳ ታንጿልና!

«/እነሱ/ እነዚያ የታገሱ በጌታቸውም ላይ የሚመኩ ናቸው።»

አል አንከቡት 59

እንግዲህ የትዕግስትን አስላማዊ እይታ ጠቅለል ባለ መልኩ እንቃኘና መቼና እንዴት እንደመንታገስ ካመላከትን በኋላ ፀረ ትዕግስት ባህሪያትን ዘርዝረን አምዱን እናሳርጋለን አላህ ከታገሾችም ያረገን ዘንድ ፀሎታችን ነው።

- ትዕግስት ለአኗህ ያለንን አምልኮ ለማድረስ የሚረዳ ቁም ነገር ነው።
- ትዕግስት የነፍስያን የውስጥ ጉትጎታ ድባቅ የሚመታ የውስጥ ጥንካሬ ነው።
- ትዕግስት ታጋሹ ወደ ላይና ወደታች የሚያሻቅብበትና የሚያሽቆለቁልበት ሀይልን አጥቶ ሀይልን የሚያገኝበት የመንፈስ ጉዞ ነው።

2. በመዝጋቢ መላኢካዎች እጅ ከፍንጅ ላለመያዝ ችግር ሲገጥም ጠንቀቅ፤ ምላስን፣ የስሜት ህዋሳትን ከመጥፎ አሳቤና ንግግር ማቀብ ከንቱ የተበሳጭቻለሁ አይነት መወራጨት መሬት ዕቃን መደብደብ ማስወገድና የቀዳና ቀድር እምነትን ማጠንከር።

መፈተን ያለና የሚኖር፤ መታገስ ደግሞ ለጀነት የሚያበቃ ነው።

«ከፍርሃትና ከርኃብም በጥቂት ነገር፤ ከገንዘቦችና ከነፍስም ከፍራፍሬዎችም በመቀነስ በእርግጥ እንሞክራችኋለን ታጋሾችንም /በገነት/ አብስር።»

አል በቀራህ 155

3. በጣም አጅ የሚየስገኘው ትዕግስት ያማረ ትዕግስት በመሆኑ ትዕግስትን በነብዩ /ሰ.ዐ.ወ/ መንገድ ማስዋብ፣
4. ትንሹ ሰብር /ትዕግስት/ የሚባል ምዕምኑ አያማርርም ሆኖም የደረሰበትን አይወድም፣
5. ሌሎች ታጋሾች በደረሰባቸው በላ/ውጣ ውረድ/ ቅር አይሰኙም በአላህ ላይ የቂን ስላላቸው አላህ ለነርሱ መልካምን መሬጭ በመሆኑ፣
6. ዋነኛዎቹ ታጋሾች አመስጋኝ ታጋሾች ናቸው ለደረሰባቸው በላ /ችግር/ ይደሰታሉ። አላህንም ያመሰግናሉ። የጠበቀ የቂን አላቸው የትዕግስታቸው ፍሬ ኢማናቸውን የሚያሳድግ መሆኑን አበክረው ያውቃሉ።

«ታገስም አላህ የበጐ ሰሪዎችን ምንዳ አያጣፋምና።»

ሁድ 115

ጉራ፣ ኩራት፣ ቁጣ፣ የአክብሮትና የእውቀት ማነስ ዋነኞቹ ፀረ ትዕግስት ባህሪያት በመሆናቸው ከአላህ /ሱ.ወ/ መንገድ እንዳያወጡን እንጠንቀቃቸው። በቁርኣንና በሃዲስ ልንፈውሳቸው ይገባል። ዲናችን ሁሌም ፈውስ አለውና!

## ለፀረ ትዕግስት ባህሪያት ፈውስ

1. እውቀት ብርሃን ነው የለውጥም ፍላጐት ያጐለብታል። የመማርን ትዕግስት ስናጐለብት የትዕግስትን ውጣ ውረድ ለመቋቋም ሀይል እናገኛለን።
2. በሐሳል ወደ ሀሳል መስራት ከመጥፎ ነገር መራቅ ለእያንዳንዱ የሐራም ጉዳና ሌላ የሀላል ቅያስ አለውና
3. ያ ትግል ድል ስለሌለ የሚገጥመንን በሚዛናዊነት ማስተናገድ የነፍስያን ውስወሳ መቋቋም የቀልብን አስተዋይነት መከተል

4. አስመታዘዝን ሐጢዓትን ስማስወገድ በጋስ ፍላጐትና በጥንካሬ መስራት፣ መጣር ወደ ተቅዋው ጐዳና የልቦና የትዕግስት ፍሬ ወደ አመስጋኝነት ሲቀየር የእዝነት ዝናብ ይዘንብና ገላን በምህረቱ ያጥበዋል።
5. መተናነስን በዕለት ተለት የኑሮ ሁናቴ ማጐልበት
6. የአላህን ኒዕማ /ፀጋ በረከት/ ማስተዋል
7. የራሳችንን ደካማ ጐን የፈፀምናቸውን ኃጢአቶች ማስተዋል

እንግዲህ የአላህ ቃል እውነት ነው። አላህ የታገሱን ያነሳል እንጂ አይጥልም መነሳትን የሚሻ ይታገስ…ያልታገሰም ወደ ትዕግስት ይመለስ። የነብዩ /ሰ.ዐ.ወ/ የጣኢፍ ውሎን ያስታውስ አዎ ትዕግስት ሰላም ነው። ሰላምም ትዕግስት ነው ከታጋሾቹ ያድርገን አሚን… ከዚያስ …ከዚያማ…
«ሰላም ለናንተ ይሁን /ይህ ምንዳ/ በመታገሣችሁ ነው የመጨረሻይቱ አገር ምን ታምር/ይሷቸዋል/»
አል ረዕድ 24

# የመጠጥ ቀውስ

አለማችን መጠጥ በሚፈጥረው ግብረገባዊ፣ ኢኮኖሚያዊና የጤና ሁናቴዎች ስትናጥ ማየቱ አሌ የማይባል ሐቅ ነው፡፡ መጠጥ በርካታ የውስጥና የውጭ ደዌ ምንጭ ስመሆኑ ወገናችን አያውቅም ቢባል የምፀት ይመስላል፡፡ የምርምር ጥረትን እንደ መቅሰፍት የማይቆጥረው ኢስላም ሳይንስ ስለመጠጥ የዘገበውን እምርታዊ ለውጥ ይቀበላል፡፡ የመጠጥ የጉዳት ሰንክሳር ከእውነት ምህዋር ያፈነገጠ አይደለምና፡፡

ክፉ (Evil) የሆነው መጠጥ ግርደፋው ምህረት-አልባ ነው፡፡ ክብር የተጐናፀፉትን - አቅልሷል፣ ጠንካራዎቹን - አክስሟል፣ ደንዳናዎቹን - አመንምኗል፤ «ሆድ ያባውን ብቅል አንዲሱ» ጠንቃቃዎችን አዝረክርኳል፣ ብዙዎችን ለአደጋ አጋልጧል፣ ብዙዎችን አናቁሯል፣ አጣልቷል፤ አያሌ ህዝቦችን ለዘማዊነት ዳርጓል፣ ሌሎችን ለአባላዘር በሽታ አጋልጧል፤ ይህ ክፉ ፈሳሽ በሚፈጥረው የውሸት አለም ሰስባ ሆነው ለቀሳፊው 'ኤድስ' ተጋልጠው ቀቢፀ-ተስፋን የጨበጡ በርካታ ናቸው፡፡

ግና የሰው ልጅ ከአውቆ አጥፊነቱ አልታቀበም፣ ይህንን ክፉ ቅይጥ ይጐናጨል፣ ይጋተራል፡፡ እርስ በርሱ ይጐነጫል - ይገታተራል - እራስን በራስ ይለበልባል እርስ በርስ ይለባለባል፡፡ 'አውቆ የተኛ ቢጠሩት አይሰማም' እንዲሉ እነሆ የአዳም ዘር ሰምቶ እንዳልሰማ አይቶ እንዳላየ ሆኖ የጥፋት ሰበዙን ይለቅማል - ሁሉም ተማሪውም አስተማሪውም፣ አዋቂውም አላዋቂውም፡፡ ፈጣሪውን የሚፈራና መልካም ግብረገባዊ ብቃት ያለው ሲቀር!

ሳይንስ የመጠጥ ጉዳት በማመላከትና መጠጥ ላመጣቸው በሽታዎች መድኃኒት በመፈብረኩ ረገድ ታላቅ ዋጋ (credit) ያለው ቢሆንም በአንፃሩ የሳይንሱ ምርምር ላለው የገበያ እሽቅድድም (Computation) በርካታ መጠጦችን በመፈብረክ ለገበያ ሲያቀርብ የሚስተዋል ነው፡፡ ህሊናን የሚሰልበው (Brain wash) የማስታወቂያ ስራ በብዙ ምሁራን ታጅቦ የማስከር ፈረሱን 'ቼ' እያለው ነው፡፡ ማን ሲያቆመው እነሆ ሽምጥ ግልቢያውን ተያይዞታል…የመጠጥ ጉጂነት በሁሉም አውታር ተረጋግጧል፡፡ በቁርኣን - በሳይንሱ፡፡ ይህንን እውነታ ለማስረፅና መለኮታዊ ፀዳልን ለመፈንጠቅ አንድ ቁርኣናዊ አንቀፅ ለአብነት ያህል እንስማና ቅውሰት ሰፋ ባለ መልኩ ይተነተናል፡፡

> «እናንተ ያመናችሁ ሆይ! የሚያሰክር መጠጥ ቁማርም ጣኦታትም እዝላምም ከሰይጣን ስራ የሆኑ እርኩስ ብቻ ናቸው፡፡ /እርኩስን/ ራቁትም ልትድኑ ይከጀላልና፡፡»
>
> አልማኢዳህ 90

<u>በፀደይ መባቻ</u>

የጀመዓው ፊት በደስታ ቢንበሸበሽም፣ አንድ የጐደለ ነገር እንዳለ ግልፅ ነው! የጐደለውን ሁሉም ያውቀዋል ግን አላስተዋለውም፡፡

ስብሰባው የአንድን - አላህ አንድነት አመላካችና ፍኖተ - ህብረት ነው! አላህ አንድ በመሆኑ ሁሌም አንድ የሚሆኑትን ይወዳል! እነሆ ታላቁ ዜና ተበሰረ የታዛው መቀናጆን ሰምቶ ሳሰማ ነጋሪት፣ አይቶ ሳሳየ አጉሊ መነፅር፣ አውቆ ለተኛ ቀስቃሽ፣ ለተራራቀ መግነጢሳዊ ቀመርን የሰነቀ የአንድነት ገመድ ነበር ስብሰባው፡፡

«የአላህንም /የማመን/ ገመድ ሁላችሁም ያዙ፤ አተለያዩም»

አል አምራን 103

በቃ አንድነትን በአነድነት፣ ለአንድነት…በአሁኑና በመጪው ትውልድ ላይ ለማስረፅ የተከናወነ የፈርስት ሒጅራ አመታዊ የፀደይ ስብሰባ! በዘላለማዊ የህይወት ጐዳና ነው የተጀመረው፡፡ በቁርኣኑል ከሪም፡፡ አላህ /ሱ.ወ/ ዳግማዊ የጥበብ ወጋግኑን በታዳጊ ወጣት ፈይሰል በሺር ላይ ይፈነጥቅ ወጣቱ ልቦናን መስጦ አጅር ተቀብሎ ለሌሎች አጅርን አስገኝቷል - ሱብሃነላህ

የመግቢያ ንግግር የህፃናት - የወጣቶች ፕሮግራም በጥሩ ሁናቴ ተከናወነ - በታዛው ስር ቢላላዊ ድምፀት ናፕ ለአስር ሰኣት ጀመዓው ፊቱን ወደ አንድዬ አቀና! ሶላቱ ሲያበቃም የማይታዋወቅ - ይተዋወቅ፣ የተጠ ፋፋው ይገናኝ ገባ፡፡ ታዳሚዎቹ ለየቅል ናቸው ህፃናት፣ ወጣቶች፣ አረጋውያን ብሎም ነፍስ ጡራን ሁሉ ነበሩ፡፡

መሪ (leader) የሆኑት ወንድሞቻችን የመሪነታቸውን ብቃት እያስመዘገቡ - ተከታዩን ይመራሉ፤ የወጣቶቹ ቡድን በክብ ጠረጴዛ ላይ ሰፍሮ ፊልም አዘል ጭውውቶችን ያከናውናል በተለይ ላኢላህ ኢለላህ የሚል ኮፍያ የለበሰው ወጣት አትኩሮትን ይስባል፡፡

ከአላህ ራህመት ምን ጠፍቶ - ብሉልኝ ጠጡልኝ ይል ዘንድ ፈርስት ሒጅራ ብፌው ዘና ብሎአል፡፡ ሴቱ ባንድ ወገን ወንዱ በሌላ ተሰልፎ የፍላጐቱን ያሳል፡፡ በገበታው ዙሪያ ውይይት ደራ፡፡ የወንድማማችነት የእህትማማችነት ቀለ ምልልስ መቼም አየበሉ አይታደር ገበታው ከፍ አለና ቦታውን የትዝታ ገበታ በጅ በደጅ አደገው!

ትላንት ህፃን የነበሩት ዛሬ አድገዋል፣ ሆኖም በፈርስት ሂጅራህ ጥላ ስር ናቸው የአስር አመት መርሃ ግብር የቪድዮ ጥንቅር ሲቀርብ ታዳሚውን በትዝታ ታንኳ አሳፈረው፡፡ ፈርስት ሒጅራዎች ያሳለፉት ረጅም ጉዞ፣ ረጅም ውጣ ውረድ የመሪዎች ያላሠለሠ ጥረት፣ ዛሬ የሚታይ እውነት ለአንድነት!

> «እነዚያ በኛ መንገድ የታገሉ፤ መንገዳችንን በእርግጥ እንመራቸዋለን፤ አላህም በእርግጥ ከበጐ ሠሪዎች ጋር ነው»
>
> አል አንከቡት 69

ቪዲዮው ሲጠፋ የክብሩ እንግዳ ኢማም ጀዋህሪ የምስክር ወረቀታቸውን ከተቀበሉ በኋላ፤ በሰብአዊ መብት ተከራካሪነትና በዳዕዋ ያካበቱትን ልምድ ያቋድሱን ጀመረ «የፈርስት ሒጅራን ህፃናት፤ ከህፃንነት ወላጅ እስኪሆኑ ድረስ አይቻለሁ» ብለው የጀመሩት ኢማም! በማንኛውም መልኩ ለሚያካሒዱት ሰብዓዊ ትግል ፈርስት ሒጅራ ከጐናቸው እንደሚቆም ሙሉ እምነት እንዳላቸው አበክረው ገልፀዋል፡፡ ቀጥለውም «ያለ ጀመዓ ኢስላም የለም» የሚለው የረሱል ሀዲስ በማከል ማህበሩ የራሱ የሆነን ማዕከል በአፋጣኝ እንዲገዛ የመላው ህዝብ ያላሰለሰ ጥረት አስፈላጊ መሆኑን ካስገነዘቡ በኋላ ዳግም ቪዲዮው ተከፍቶ የወጣቶቹ መልእክት ይሰማ ጀመር!

«ርዱን» ይላሉ ወጣቶቹ! «ርዱን ማዕከሉን ግዙልን እና አደንዛዥ ዕፅን፣ መጠጥን፣ ዝሙትን እምቢኝ ብሎናል! የማዕከሉ ጉዳይ ለኛ ብቻ ሳይሆን ለቀጣዩ ትውልድ አንገብጋቢ ነው በማለት ህዝቡ የትኩረት አቅጣጫውን እንዲያሰፋ እያመላከተ ነበር፡፡

ይህን የሰሙት ኢማም የመዋጮውን ሂደት ያቀላጥፉ ጀመር ሁሌም ከሙስሊሙ ዑማ ብዙ ቢጠበቅም ያለውን የሰጠ ንፉግ አይባልም እንደሚባለው አልሃምዱሊላህ መዋጮው - ማሼ'ያ

ለመግዛት ለስታቀደው ህንፃ በቪዲዮ የተደገፈ ዘገባ ያቀረበው ወንድም አብደሏህ ሁሉም ሃላፊነት እንዳለበት፣ ሁሉም መጣ ግዴታው እንደሆነ የምሁራን ችግር እንደሌለብን ዶክተሮች አንጂኒየሮች እንዳሉን አመላክቶ ነበር፡፡

በምርምር ስራው አድናቆትንና ዝናን እያተረፈ የመጣ ኢትዮጵያዊ ሙስሊም ሳይንቲስት ዶክተር ዘኪ ሸሪፍ ነፍስያውን አሸንፎ ለሚያደርገው ኢስላማዊ አስተዋፅኦ በጀመዓው መሪ ተመስግኖ የምስክር ወረቀቱን ሲቀበል፤ ሌላው በዓለም ላይ ለሚገኙ አትዮጵያውያን ሙስሊሞች ብቸኛው አንደበት የሆነው የፈርስት ሒጅራ የራዲዮ አገልግሎትና አዘጋጆቹ ለበጐ አድራጐታቸው የምስክር ወረቀቱን ተችረዋል፡፡ ወንድም ነጂብና ኑሩ ይህንን የአንድነትና የመሪነቱን ሚና ተጫወተ ከመግሪብ በኋላም ስብሰባው ተዘጋ፡፡ አዎ! በአላህ መንገድ ለመሠማራት ብሎም ሰውን ወደ ሠናይ ምግባር ለመጥራት ቦታ ለደት አይወስነውም፡፡ በአላህ ዘንድም የተወደደ ምግባር ነው፡፡ ለዚያ ነው አላህ /ሱ.ወ/ በቃሉ እንዲህ ያለን፡፡

«እነዚያ ያመኑት፣ ከአገራቸውም የተሰደዱት፣ በገንዘቦቻቸውና፣ በነፍሶቻቸውም በአላህ መንገድ የታገሉት አላህ ዘንድ በደረጃ በጣም የላቁ ናቸው። እነዚያ እነርሱ ፍላጐታቸውን ያገኙ ናቸው»

አልተውባህ 20

ይህ የአንድነት ጥሪ ፍፃሜው ያማረ ሆኖ የጀመዓው ፊት በደስታ ቢንበሻበሽም አንድ የጐደለ ነገር እንዳለ ግልፅ ነው። ሁሉም የጐደለውን ያውቀዋል ግን አላስተዋለም። ታዲያ ምንድን ነው ጃል? ትሉ ይሆናል! የአይናችን ብርሃን ለዱንያም ይሁን ለአኼራ የተስፋ ነፀብራቅ የሆኑት አባት ሙፍትህ ሙሐመድ ስራጅ! የአላህ አገልጋይ ናቸውና ከኢትዮጵያ አላህ በሰላም ይመልሳቸው አሚን!

ታዲያ ለምን እንደዚህ ሁሌ አንሰባሰብም? ለአላህ ብለን ለምንስ በአላህ ጉዳና አንሳተፍም? አላህን እንፍራና ከዱንያ ስንክሳር እራሳችንን ነፃ እናውጣ ለኛ ከኛ ሌላ ማን ሊመጣ! ድር ቢያብር አንበሣን ያስር ብለን እንውጣ! ያማረ ይሆናልና የኛ ዕጣ!…የተስፋ ቃሉን እነሆ!…

«እናንተ ያመናችሁ ሆይ አላህን ፍሩ ወደርሱ መቃረቢያ /መልካምን ስራን/ ፈልጉ ትድኑ ዘንድም በርሱ መንገድ ታገሉ።»

አልማኢዳህ 35

## ህይወትን በአቻ

ትዳር በወንድና በሴት መካከል የሚመሰረት ቅዱስ ግንኙነት ነው - በኢስላም፡፡ ተጋቢዎቹም አንዳቸው ለአንዳቸው የተፈቀዱበት፣ ትብብር፣ መቻቻል መፅናናት፣ መደሰት፣ ልብ ለልብ መገናኘት የሚሰፍንበት ፍቅራዊ ጥምረት ነው፡፡

ሁለቱም ጾታዎች በላህ /ሱ.ወ/ መንገድ ሲጣመሩ በፍቅር፣ በመግባባት በመተባበር ፅኑ ኢስላማዊ ቤተሰብ በመመስረት የአብራክ ክፋይ የሆኑት ልጆች የሚያሳድጉበት፣ በጐ ፀባይን የሚቀስሙበት፣ ኢስላማዊ መንፈስን የሚያጐለብቱበት በረከት አዘል የህይወት ጉዳና ነው - ትዳር፡፡

ቤተሰብ ለኢስላማዊ የአኗኗር ዘይቤ ብለም ለኢስላማዊ ማህበረሰብ ግንባታ ታላቅ አስተዋፅኦ አለው፡፡ ምክንያቱም የቤተሰቡ አባላት የሚረዳዱ፣ የሚተጋገዙ፣ የሚጠቃቀሙ ሆነው ወደአንዱና ቀጥተኛው የአላህ ጉዳና እርስ በርስ የሚመራሩና ብሎም የሚማማሩ ናቸውና፡፡

ጋብቻ በኢስላማዊ የአኗኗር ዘይቤ ሲታነፅ፣ ኢስላማዊ ስርዓት በመንታ ልቦና ላይ አምዱን ሲቀርፅ የጥሩ ሴት ብልሃትና ዝየዳ ህይወትን ለስኬት የሚያበቃ የተስፋ ምርኩዝ መሆኑ አሌ የማይባል ሐቅ ነው፡፡ ስለምን ቢሉ መልካም ሴት ለኢስላማዊ ቤተሰብ የጀርባ አጥንት ናትና፡፡

ከብዙ እልህ አስጨራሽ ለመኖር ከሚደረግ ውጣ ውረድና ድካም በኋላ መፅናናትን፣ መረጋጋትን፣ ልዩ እረፍትን ለጋሽ መሆኗን አላህ /ሱ.ወ/ በቁርኣን ከሪም ላይ ጥርት ባለ መልኩ አስቀምጦታል፡፡

> «ለናንተ ከነፍሶቻችሃ /ከጐሶቻችሁ/ ሚስቶችን ወደ እነርሱ ዘንድ ትረኩ ዘንድ መፍጠሩ በመካከላችሁ ፍቅርና እዝነትን ማድረጉ ከአስደናቂ ምልክቶቹ ነው፡፡ በዚህም ውስጥ ለሚያስተውሉ ተዓምራቶች አልሉ፡፡»
>
> አል ሩም 21

ፃድቃን በእጅጉ መልካም ቤተሰብን ይገነባሉ ስለምን ቢባል ግንባታው ለኢስላማዊ ፅናትና ስምረት ጉልህ መስተፀምር ነውና፡፡ ይህ ዲናችን በወደር የለሽ መዛግብቱ ቤተሰብን አስመልክቶ በአያሌው ዘግቧል፡፡

ዘገባውም ምጥቀትን እንደ ጳኖ የደረበና ፋና ወጊነቱን በአይቀሬ እውነታ ከዘመናት ወደ ዘመናት ቢያበስርም የሰው ልጅ ገቢራዊ ኑሮ በመጤ የዱንያ ሰደድ ይንቦገቦግና የውር ድንብር ጉዞውን ይኳትናል፡፡ ፈርም ይስታል በስስት የተሞላን የውስጥ ስሜት ይከተላል አለማዊነቱን ብቻ ያሎላል መንፈሱን ያደኸያል እራሱን ከመንፈሱ ይነጥላል፡፡ በአለም ሰደድ ይበግናል ይጨሳል መፍትሔ በመፃፉ ጨብጦ ግራ ይጋባል እንዴ

ቢሉ ሰላማዊነትን መንፈሳዊነት ሲነጣጠሉ የማይችሉ ገፅታዎች ናቸውና...ግር አይሰኙ...ፍኖተ ህይወቱን ይቃኙ...መዛግብቱ በመንታ አይኖ ይጐብኙ...መንፈስን ከሰለም እንዲያገናኙ...።

ኢስላም ፍኖተ ህይወት ነው መንፈሣዊነትና ሰላማዊነት በፍፁም ሊነጣጠሉ የማይችሉ ጣምራ የመኖር አልያም የመሞት ዘይቤአዊ ስርዓት ናቸው። ለምሳሌ በእስልምና ሰለም በቃኝ ብሎ መመነን የተከለከለ ነው። ሰላማዊነት መንፈሳዊነት፤ መንፈሳዊነት ደግሞ ሰላምአዊነት ነውና ሰላምበቃኝታው ተራክቦን ለማስወገድ ከሆነ ተራክቦ በአያሌ ነብያትና ፃድቃን መፈፀሙ የማይካድ ነው። በሌላ መልኩ ይህ ከፀያፍ ዘማዊነት የምንታቀብበት የመውሰድ የመዋለድ ፅንሰ ሃሳብን የምንተገብርበት በበረከቱ ልዩ ደስታን የምንጋራበት ሂደት እንደ ኃጢዓት ሊቆጠር መስተዋሉ አይካድም። ግና ተራክቦን ካልተፈቀደ ሰው ጋር ማድረጉ፣ ወይም በተከለከለ ግዜና ቦታዎች መፈፃሙ እንጂ ይህንን የአዳም ልጆች የእስትንፋስ ምንጭ የኃጢዓት መለዮ ሊሰብስ አይገባም። አሳህ /ሱ.ወ/ ለምን ተቃራኒ ጾታ አድርጐ እንደፈጠረን እናስተውል።

«ከነርሱም ሁለት ዓይነቶችን ወንድና ሴትን አደረገ»
አልቂያማህ 39

እንግዲህ የዚህ ከሃሲ አምላክ ቸርነት ተወስቶ የማያበቃ ነው። የፈቀደልንን የፈጠረልንን ህግጋቱን ሣይፕሱ መፈፀም ግዴታ ሆኖ ሳለ ተግባሩን ኃጢዓት በሚል ቅፅል ስም መጥራቱ ግራ ያጋባል። ሰለም በቃኝ ማለቱም ተፈጥሮን በሌላ ቅርፅ ለመከየን የሚደረግ የራስ በራስ ተቃውሞ ይመስላል። ሁሉም እራሱን ይመልከት የፍትወት ጠብታ ግኝት መሆኑን የሚክድ አይገኝማ።

ሰውን ከፍትወት ጠብታ ፈጠረው።
አል ነህል 4

ጋብቻ በአቿ ጋብቻ መባዣ መደሰቿ ጋብቻ በአሳህ መንገድ ብቻ የሚለው ፅንሰ ሃሣብ በህብረተሰባችን የመኖር አድማስ እንዲሰርፅ ፀሃፊው የግል ጥናቱን በማካሔድ አንኳር የኢትዮጵያውያን ችግርን ሲያመላክት ይወዳል ከስህተት የጠራው አምላክ ከስህተት እንዲጠብቀው እየተማፀነ ነው።

1. እያፈቀሩ መጥፎ ሲሰሩ

ፍቅር እራስን ሁለንተናን ለሌላው አሳልፎ የሚሰጥበት የመስዋዕትነት ጉዳና ነው። ማፍቀር ለጠንካራና ለደካማ ጉን ነው። በድሎት ግዚያት ድሎትን መጋራት፣ በጥንካሬ ወቅትም አብሮ መጠንከር ብሎም ድካምን ችግር ሲፀናወት አልበገር ባይነትን ማሳየቱ የእውነተኛ ፍቀር ዘላለማዊ ተምሣሌት መሆኑ ሊካድ የማይቻል ሐቅ ነው።

ማፍቀር በጥቅሉ ስተሣካ ትዳር ጥርጊያ ጉዳና ይሁን እንጂ መስማማት ካልታከለበት ደስታን እንደ ጤዛ ያረግፋል፤ ፍቅርን ትዳርን በአጉሊ መነፅር ለይቶ ልዩነታቸውን ማጤኑ ብልህ ያስብላል ስለምን ቢሉ ፍቅር ጋብቻን ትዳርን የሚያጌጥ ልባዊ ፈርጥ ነውና፡፡ ፍቅር በሁለቱ ተጋቢዎች ላይ የሚገኝ ሲሆን ጋብቻ ግን የሁለቱንም ቤተሰቦች የሚያጣምር ዘመድ አዝማድን የሚያካትት ትስስር ነው፡፡ አምዱን ለማሣጠር ስለሚዋደዱ ስለሚፋቀሩ መጥፎን ቢሰሩ በማስቀናትና በማስፈራራት ፍቅርን ዋጅቶ ትዳርን ለማጠንከር ከጣሩ …የበዋልፈሰስ ክምርን በኑሮ ሳይከመሩ …ያን ያማረ ትዳርን አሻከሩ…ጋብቻውን በጠበጡ…ፍቅሩን ብቻ ጨበጡ…መፋቀር መዋደድ በትዳር ህይወት ለመኖር ብቻውን በቂ አይደለማ…ስንቶች እየተፋቀሩ ታይቷል፡፡ ሲስያዩ ስለዚህ ልብይበሉ …መጥፎ በጥሩ እንጂ በመጥፎ አይገራም

2. መፎካከር ቂም ይዞ ማደር /ነፍስያ/

ጥሩ ለማድረግ መፎካከር ሲያሳፍር፤ ጥሩነት የማይከፈልበት ፀጠራ ልቦና ነፀብራቅ ነው፡፡ እርሷ ጥሩ ከሰራች እኔ ሰራስሁ እርሱም ጥሩ ከሰራ እኔ ሰራስሁ ማለት መኮራረፍ ካስ ቀድሞ አንዱ እስኪያናግር መጠባበቅ ወዘተ. ያለመብሰል ምልክት ይመስላል፡፡ በፀሃፊው አመለካከት ቀድሞ ጥሩነትን የሳየ በዱንያም ይኹን በአኼራ በላጭነቱ አይጠረጠርም፡፡ ቂም ይዞ አኩርፎ ከማደር ዛሬውኑ መነጋገር ውይይት ፀብን የሚፈውስ ፍቱን መድኃኒት ነውና የሚፈጠረውን ችግር በወቅቱ ካልተነጋገሩ ኢምንቱም ይገዝፍና ለስላሣውም እንደ አሎስ ይጠነክርና አዕምሮ ለመልካም ነገር ቦታ አጥቶ በነገር ቅራንቅንቦ ተሞልቶ ይጠባል፡፡…ከዚያ ጠባብ ያደርጋል ቦታ ሲጠብ ስፋት ይፈስጋል በሌሳ አነጋገር ሁለቱንም ያስያያል ተጣበዋላ

3. እራስን መምሰል

እራስን መምሰል እራስን መምሰል በራስ የመተማመን ገፅታ ነው እንዴት ቢሉ የራስ ያሉት የራስ ነውና እንደነ አከሌ ሳይሆን እንደ እራስ ይኑሩ ዛሬ አከሌን ነገ አከሊትን መምሰል ከፈለጉ እራስን እራስነቶን ፈልገው ያጡትና ግራ ይጋባሉና ልብ ይበሉ የቤት ዕቃዎን፣ መኪናዎን፣ ስራዎን፣ ትምህርቶን፣ የዕረፍት ጊዜዎን ሌላንም እንደቤቶ ያድርጉት ግና ከጐረቤቶ መልካምን ይቅሰሙ ጥሩ አርዓያነትም ካለ ይከተሉ፡፡ ሰው ለሰው መድኃኒት ነውና…ቢሆንም ሰው ለሰው አጥፊ መሆኑን አይዘንጉ ስለዚህ በአቋም ላይ ፅናት በድርጊቶ ላይ ጥራት በሙያ በእውቀት ዘርፎ ብቃትን በጅ በደጅ ያድርጉ…ሁሌም እራሶን መሆኑን እራሶን መምሰሎን አይዘንጉ

4. ምስጢርን መጠበቅ

ምስጢር ዘላለማዊ ቃልና የእምነት መተማመን ችሎታን አብሳሪ ነው፡፡ ምስጢር ማለት የውስጥ ሲሆን የውስጥ ገላ በአይኑ ብሌን ማየት እንደማይቻለው ሁሉ ምስጢሮን እራሶ በራፌ ካላወጡት የውስጥ እንደሆነ ይቀራል፡፡ ምስጢር የአስተዋይነት ገቢራዊ ትዕይንትና ያበቅ የለሽ የለት ተለት ፈተና ነው፡፡ ...ነገር ሲያመልጥ ፀጉር ሲመለጥ... እንዲሉ እንደበቶን ቆንጠጥ ዙሪያ ገባውን ጉል ጠንቀቅ ገልመጥ...በዘመናችን ብዙዎች በሰው ቁስል እንጨት ሰደድ አይነት ስለሆኑ ነቃ ግዴታ ካልሆነና ምርጫ ካላጡ በስተቀር የክት ምስጢሮ በወንፊት የተቀመጠ ውሃ ሳይሆን ካዝና የተቆለፈበት አልማዝ ይሁን...አልማዜ ይበልት ምስጢሮን፡፡

ምስጢሮት የሚጠፋው ባፍ ይጠፉ በስፈለፉ ዓይነት ብቻ ሣይሆን የገላዎት ቋንቋም አንዳንዴ ሲናገር ስለሚችል አላስመሳጊ የሆነ መመናጨቅ፣ መኮሣተር፣ መቄጣት ማደናበር መኩራት መሞላቀቅ አጉል ትዕዛዝን በሰው ፊት አያድርጉ ትዳሮን ነቅንቀው ያላሉታልና...ባለቤቱን ካልናቁ አጥሩን አይነቀንቁ ይባል የለም እርሶም እንዳይናቁ በሰው ፊት አይባርቁ የግል ምስጠ ሮን ለሌላ አይዘባርቁ ይጠንቀቁ

5. ስልጣኔ ወይስ ሰይጣኔ

የሳት እራት መብራት በጉላበት ዙሪያ ትበርና እራሷን አንጣጥታ ትጠፋለች በስደት ለምንገኝ ወገኖች ወይም በእናት አገር ላይ ስልጡን መባል ስምንሻ ስልጣኔ ብለን የምንቧርቅበትን ጉዳና ልብ እንበለው በራሣችን አንተማመን ምክንያቱም ሃይማኖታችን ከ1400 ዓመት በፊት የደመቀ የስልጣኔ ወጋግን ነውና ስለዚህ እራሣችንን በፅኑ እንውደድ ያለንን እናክብር ከሌላው ዓለም መማር፣ ማወቅ መልካምን መቅሰም ካለብን በወጉና በሚዛናዊነት ይሁን - ሁለት እግር አለኝ ተብለ ሁለት ፈረስ ላይ ስለማይወጣ ያንን የምንጋልብበትን የነፍስያ ፈረስ ወደ አንድዪ መንገድ ቸ! እንበል፡፡ ይህ ካልሆነ ስልጣኔ እየመሰለን ስልጡን ስመባል እየተቻኮልን የምናደርገው የውር ድንብር ጉዞ ሰይጣኔ ይሆናል ሰይጣን ደግሞ የሳት በመሆኑ የሳት እራት ላለመሆን ረጋ ሙያ በልብ ነውና!

6. ትዳርና እጮኛነትን ማደባለቅ

እጮኛነት ሁለቱ ግለሰቦች ለትዳር እንዲበቁ የሚተጫጩበት ወቅት በመሆኑ ሁለቱም ጥሩ ስመሆን እንደሚጥሩ ግልፅ ነሰ፡፡ ያላቸውን ደካማ ጉን በመደበቅ ፈተናውን ስማለፍ ይታገላሉ ከዚያም ይጋባሉ፡፡ አንድ አካል አንድ አምሣል ስመሆን ይጥራሉ፡፡ ከመሆኑም ጋር ከደካማ ጐናቸው በውስጥ የሰነቁትን ወደትዳሩ ይዘው መንዛቸው አይቀሬ ነው፡፡

ብዙ ወገኖች ትዳር ሮጦ የሚገባበት የገነት ዳርቻ ይመስላቸውና ሲጀምሩት ግራ ይጋባሉ፡፡ ትዳር ሁለት የተለያየ አመለካከት አስተሣሠብ፣ አስተዳደግ፣ ዕድሜ፣ ብሎም የእውቀትና የትምህርት ልዩነት የላቸውን ሰዎች አንድ የሚያደርግ ጉዳና በመሆኑ እንቅፋት ያጣዋል ማለት አይቻልም፡፡ ስለዚህ እንቅፋቱን ይፕረጉ ልዩነቱን ያጥቡ የትዳርን ምንንነት ይገንዘቡ አንድ ለመሆን ይጣሩ ይታገሉ ይጣመሩ የድካምን ውጤት ሲጉናፀፉ ፈተናውን አስፉ ፈተናውን ስማስፍ ተስፋ አይቁረጡ ወርቅ በእሣት ካልተፈተነ አፈር መሆኑ አይዘንጉ ትዕግስትን ይላበሱና ይበርቱ.. ከሁለት በላይ ሲሆኑ...ልጅን በአሳህ ሲወፈቁ ትዳሮት አይቀርም መጥበቁ ታዲያ ሳጥር ህይወት መመካከር መወያየት መቀራረብ ማገናዘብ እጮኝነትንና ትዳርን አብጠርጥሮ ማወቅ ለመታረቅ፡፡

7. ድብብቆሽ

አንዳንዶች የቅርብ ሩቅ ናቸው አብረው እየኖሩ አብረው እየበሉ እየጠጡ አይተዋወቁም ያሁኑ ይባስ አብረው እንዲለ እየተኙ አይተዋወቁም ምንድነው የሚያውቁት በገበታው ዙሪያ ተኝተውም ይሁን የሚያስቡት በተለያየ የሃሣብ ባህር መንጉዳቸውን ነው...ባለ እንዳይሰማ...ሚስቱ እንዳትሰማ ማለቱን ያበዛለ እንደውም ሰው ከትዳር አጋሩ ደብቆ ከሌላ ይወያያል፡፡ ስለዚህ በሃሣብ መለያየቱና መደባበቁ ከሶስተኛ ሰው ጋር መዘላበዱ በትዳሩ ላይ ንፋስ አስገብቶ አቻነትን ይነፍገዋልና ግልፅ ይሁኑ የቆጡን አወርድ ብላ የብብቷን ጣለች አይነት አይሁኑ እራሶን የጢኑ እራሶን አንዳንዴ ይጠርጥሩት ያልጠረጠረ ተመነጠረ ይባላል የሲ

8. ምክንያት ማስተባበል ማሣበብ

እንዲህ ቢሆን ኖሮ እንዲህ አይሆንም ነበረ የሚሉት ቅብጥርጥርታ...የግትርነት ገፅታ...የበላይነት ከንቱ ስሜት ፌሽታ...ቁም ነገር የለሽ ድንግር ግርታ...የነገር ታርጋ ዝውውር ውረታ...ምክንያት ማስተባበል የሚሉት ዋይታ

ምክንያት በዘልማድ ጥፋትን የምኖ ሳለመቀበል የሚገነባ ቅርፊት ነው ይህም ጥራትን የሚያዘቅጥ አዕምሮን ለድንቁርና የሚያገልጥ መጥፎ ባህሪ በመሆኑ ጥፋቱን በማመን ፈንታ ምክንያት የሚደረድር ካለ የሚያሣብብ የሚያስተባብል ካለ መሻሻልን ፀጠላ አውቆ ጅል ነው አውቆ ጅል እያየው የያዘውን ያጣል ያጣው ደግሞ ያቃጥለዋል ያብከነክነዋል ስለዚህ ከምክንያት ከማስተባበል ከማሣበብ እውነቱን ተናግሮ የመሸበት ማደር...ጥፋትን አምኖ መሻሻል ለመሆኑ ለሚያስተባብለ አላህ /ሱ.ወ/ በሱረቱል አልረህማል ላይ ስንቴ እንደጠቀሰ ልብ አላሉምን

9. ውሸት ማዋሸት መወሻሸት

የእውነት ደግነቱ በተደጋጋሚ ሲያስታውሱት አይገባም፡፡ የውሸት ክፋቱ በእያንዳንዱ ሰዓትና ደቂቃ መታወስ አለበት፡፡ መዋሸት የተከለከለና ኃጢዓት ነው፡፡ ረሱል /ሰ.ዐ.ወ/ ውሸት የተከለከለ ነው ቅንጣት ታህል እንኳ ቢሆን ብለዋል፡፡ አላህም በተለያዩ የቁርኣን አናቅፅ ወዮላቸው ለዋሾዎች በማለት አስጠንቅቆናል፡፡ እውነት ልባዊ ብቃት ሲሆን ውሸት ደግሞ ሚዛን አልባ እንደበታዊ እስትንፋስ ነው፡፡ ሐሰት ግምትን ያስቀንሳል ክብርንም እፍ ሲለት ጭልጥ አይነት ያደርጋል ያዋርዳል ያቀላል ሰብዓዊነትንም በሾተለ ይጨቀጭቃል ለምን ይዋሻሉ?...ለምንስ በገዛ እጆ ይዋረዳሉ..ሙክት ሲጠግብ ሾተል ይልሣል አይነት ለምን ይሆናሉ...ዋ ወዳጄ ልብ ይበሉ ከንቱን ዋሽተው ስንቱን አስታውሰው ይችላሉ? እርሶ አድገዋል ትልቅ ሰው ኖት ለምን ይፈራለ መዋሸት ፈሪነት ነውና ዛዲያ...እውነቱን ተናገሮ የመሸበት ማደር የሚለው የወኔ ቃልሣ እንዴት ይረሣ...አይ የትውልድ አበሣ በመዋሸት ሚሙቶ ሲሆነው ኮሣሣ ...የአበው ተረቱ ቃስ ነበር ብርቱ...እውነትና ንጋት አድረው ይጠራሉ...በማለት መዛቱ በቅጥፈት ነበልባል ነፍሶን አይጥበሱ...እውነትን በእውነት ሁለ ይጠንስሱ...እራሶን ያስታውሱ...አላህን አይርሱ...እርሱ እውነት ነዋ...ቀጠሮው እውነት ነዋ...ቀጠሮው ነዋ...ገነት እውነት ነዋ...ገሃነም እውነት ነዋ...ሞት እውነት ነዋ...ሙሃመድ /ሰ.ዐ.ወ/ እውነት ናቸው...ቁርኣን እውነት ነዋ...ታዲያ ለምን ይዋሻሉ...ይወሻሻሉ...ምላሶን በጥርሶ ሞርደው ለምን ይቀጥፋሉ...ዲዳን አላዩማ ምላሱን ተይዞ...መናገርን ሲጥር ጣቱን ተመርኩዞ በጭንቀት በጥበት እራሱን ወዝውዞ...እኮ ለምን ይዋሻሉ...ያልሆነን በምላሶት ለምን ይስላሉ...እውነት ነው እያለ ለምን ይምላሉ...ዋ ስርሶ ከዋሹ...አኼራዎን ዱንያዎን አበላሹ አሳማሚ ቅጣት ነው የነገ ምላሹ...ልብ አድርጉልኝ በአንድዬ ዛሬም ይሁን ሁሌ...እኔ ጠቅሻለሁ የዋሾን ምሳሌ...የስመዱት ልማድ ያሣድዳል ከማድ እንዲለ ዋሾ ይዋሸኛል አልሰማሁም ብሎ...እራሱን በራሱ በቃሉ አታሎ...እርሶ ግን ልብ ይበለ ልብ ያለው ልብይላልና

10. አልባሴ ቦታ

ትዳር ይዞ መዝረክረክ እዚም እዚያ ማለት ቤትን ሸሽቶ የሰው ቤት ውጪን መውደድ የትዳርን አትኩሮት ነፍጎ የመዞር፣ ሱስ ማናር የሰው ቤትን የሞቀበት ማሞቅ እዚም እዚያ አለሁ አለሁ ማለት አንዳንዴ እንደ ሱስ እንደሚያንገበግብ ይስተዋላል፡፡ ባል ከሚፈቅድበት ቦታ ውጪ፣ ሚስት የምትስማማበት ቦታ ካልሆነ በየቦታው ማውደልደል ተገቢ አይደለም፡፡ ውጪ ሙስ በሙስ ሳይዘነጋ ከአልባሴ ቦታ ርቆ የትኩረት አቅጣጫን ወደ ትዳር ማረጉ ብልህነት ነው፡፡...ሁለ አማረሽን ገበያ አታውጧት እንደሚባለው ፅኑ ምርጫ ያከናወኑ ትዳር ቤቶን ወይስ እዚም እዚያ...በፅሁፉ መግቢያ ላይ እንደተጠቀሰው ቤተሰብ ለኢስላማዊ የአኗኗር ዘይቤ ብሎም ለእስላማዊ ማህበረሰብ ግንባታ ታላቅ አስተዋፅኦ እንዳለው አይዘንጉ ቤተሰቦን በንስር ዓይን ይመልከት መከታተል መንከባከብ ትዳርን የተሳካ ከሚያደርጉት መልካም ጉዳናዎች አንዱ

ነውና፡፡ ይንቁ ቅድሚያ ሚቴን፣ ባለን፣ ልጆችን …እራሶን ቤተሰቦን ሐይማኖትን ጥሩ ቤተሰብን መገንባት ሐይማኖት ነውና…

ይኸው ቃሌንም ጠብቂያለሁ የኪነጥበብ ሒጅራዬንም አድርጌአለሁ ከወርቃማው ማይክራፎን በስተጀርባ እገኛለሁ…አልሃምዱሊላህ…እኔው ነውነኝ የምታውቁኝ…ልብ ያለው ልብ ይበል ባዩ ለማታውቁኝ ደግሞ የካንሣስ ሲቲው ሳዲቅ አህመድ የናንተው ጀማዓ ሆኛለሁ የምፅፈውን እንድተገብር ዱህ አድርጉልኝ…

አለማወቁ ን የማውቅ የህይወት ተማሪ ነኝ አላህ ከኒፋቅ ያጠብቀኝ በዕሬ ወደ ቀናው ጉዳና ወደኸይር የምትጣራ ያድርግልኝ…ስነፅሁፌም…ዘገባዬም…ቅንብሬም…ለአለማት ጌታ ነው እላለሁ…በል ብሎኛላ…ቃለ በቁርኣን ያ በብዕር ያስተማረ ይላላ…እኔም ከልቤ ልበለው ልብ ያለው ልብ ይበል እንደምለው…

ስግደቴም መገዛቴም ሕይወቴም ሞቴም ለአለማት ጌታ ለአላህ ነው በል

አል አንዓም 162

## የጥርስ መፋቅ ትዕይንት

ሁሉም በነፍስ ወከፍ የጥርስ ብሩሽ ጨብጦ ጀርሞችን ለመደምሰስ ቆርጦ የተነሳ ይመስላል፡፡ የት ነው ካሉ ቻይና! ምን ያህል ሰው ወጣ? 10240 የሚሆኑ የቻይና ተማሪዎች ለምን? «ብሔራዊ የአፍ ጤንነትን ቀን»ን በመመርኮዝ! መቼ ሲሉ ደግሞ Sep. 20-2003፡፡ አጃኢብ

ተማሪዎቹ ሪከርድ ቢሰብሩም ቅሉ ዘጋቢዎቹ የዘነጉት ነገር ቢኖር በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሙስሊምች በቀን ውስጥ በየፀሎት ወቅትና ከፀሎት ውጪ ጥራሳቸውን በተደጋጋሚ መፋቃቸውን ነው፡፡ እንዴት ካስ መፋቂያ ነበብዩ ሙሃመድ /ሰ.ዐ.ወ/ ሱና /ፈስግ/ ነውና!

* * *

## ረጅሙ ነፍስን መሣት

የተኛችዋ ውቢት በመባል ትታወቃለች ከዚሁ ከፍሎሪዳ ነበረች፣ ኢሌኒ አስፖኪቶ ትባላለች ብቸኛ የናትና የአባቷ ልጅ ነበረች የትርፍ አንጀቷን ለማስወገድ የተወጋችው የማደንዘዣ መርፌ በAug. 6 -1941 ነበር፡፡ በወቅቱ የስድስት አመት ህፃንም ነበረች፡፡ ነፍሷን እንዳሳተች በNov. 26,1978 ከዚህ አለም በሞት ስትለይ ዕድሜዋ 43 ዓመት ከ357 ቀናት ነበር፡፡ ለ37 ዓመት ከ111 ቀናት ያለማቋረጥ ነፍሷን መሳት አጃኢብ! አያስብልም? ታዲያ እርሶስ አላህ ለሰጦት ጤንነት አያመሰግኑትም?

ሰባት ህፃናትን በአንድ የምጥ ወቅት የተገላገለች እናት፤ ሐስና ሙሃመድ ሁመይር ትባላለች፤ በ40 ዓመቷ በአብሃ ከተማ በአሲር ግዛት /መንጠቀተል አሲር/ ሳውድ አረቢያ ውስጥ ነው ያማጠችው፡፡ ምንም የማይሳነው አላህ ተዓምሩን አሳየባት 4 ወንድ 3 ሴት በJan 14/1981 በሰላም ትገላገላለች፡፡ ትንሹ ህፃን 2 ጠውንድ ይመዝን ነበር - ታዲያ አጃኢብ አይደለምን

* * *

## ረጅሙ ማስነጠስ

እነሆ የአለርጂ ጊዜ ከተፍ ብሏብ አይን ያሳክካል ውና ይቋጥራል አፍንጫ ያስነጥሳል ጉሮሮ ይበላል ጆሮን ያሳክካል የሚያስነጥሶት እንደሆነ ልብ ይበሉ - ይኸኛው የጉድ የማስነጠስ ገጠመኝ ነው፡፡ እንግሊዛዊቷ ዶና Griffiths በJan 13/1981 የጀመራት ማስነጠስ በዓመት ሲሰላ አንድ ሚሊዮን ግዜያህል ይሆናል፡፡ Sep. 16 1983 ያለማስነጠስ ያረፈችበት ቀን ሲሆን 978 ቀናትን በተከታታይ በየአምስት ደቂቃው ልዩነት አስነጥሣ ነበር ማለት ነው፡፡ ይህችን ያለራ ሁለት አመት ወጣት ያበሣጫት ነገር ቢኖር ከምትወደው ዋና መቋረጧ ነበር፡፡ ሌላኛው አጃኢብ! አይሆንም

*                    *                    *

<u>ትልቁ ትርፍ አንጀት</u>

በJune 11 2003 የ55 ዓመት ከሆኑት ጠኪስታናዊ የተወገደው ትርፍ አንጀት እርዝማኔው 23.5cm /9.2 in/ እንደነበር በጂነስ የአለም መዝገብ ተዘግቧል፡፡

*                    *                    *

<u>ክርስቲያናዊ ያልሆነ ታላቁ ሀይማኖት</u>

በ1999 እ.ኤ.አ. 1.16 ተከታዮች የነበሩት፣ ሀይማኖቱ ከአረቢያ ቢጀምርም 80% የሚሆኑት ተከታዮች ከአረቡ አለም ውጪ የሚገኙ፣ በፍጥነት እያደገ ያለ ሀይማኖት ማን ነው ቢሉ የጂነስ መዝገብ ኢስላም ነው ይሉታል፡፡

*                    *                    *

<u>የአለም ወፍራሙ ሰው</u>

ጃን ብራወር ሚኖች ከ1941-83 ሲያትል ዋሽንግተን ውፍረትን ከህፃንነት ጀምሮ የተጐናፀፈው ይህ ግለሰብ በ1978 ውፍረቱ ከ635 ኪ.ግ. በላይ እንደነበር ተዘግቧል፡፡ እርሱን ሆስፒታል ለማድረስ ተሻሽሎ በተሰራ ቃሬዛ ላይ አንድ ደርዘን የእሳት አደጋ ሰራተኞች የተሠማሩ ሲሆን ሆስፒታል ከተኛበት አልጋ ላይ እርሱን ገልበጥ ለማድረግ ብቻ 13 ሰዎች ተረባረቡ፡፡ ከሁለት አመት በኂላም ከሆስፒታል ሲወጣ ክብደቱ 216 ኪ.ግ. በመሆኑ በሰው ልጆች ታሪክ ውስጥ የታየ ትልቅ የውፍረት መቀነስ ተብሎ ተዘግቧል፡፡ ዳሩ በOct. 1981 ሌላ 89 ኪ.ግ. በመጨመሩ ወደ ሆስፒታል ገብቷል፡፡ በSept. 10 1983 ከዚህ ዓለም በሞት ሲለይ ክብደቱ ከ362 ኪ.ግ. በላይ እንደነበር በጂኒየስ መዝገብ ተዘግቧል፡፡

*                    *                    *

<u>ረጅሙ መኪና</u>

ግማሽ የእርግ ኳስ ሜዳን ለማከል ይቃረባል፡፡ እዚሁ ካሊፎርኒያ ውስጥ ነው የተገነባው ቁመቱ 30.5 ሜትር ወይም 100 ጫማ ሲሆን የመዋኛ ቦታ king-size አልጋ አለው - አጃኢብ

*                    *                    *

<u>ሆዳሙ - አጥፊው በራሪ ነፍስ</u>

ቁመቱ ከ4.5cm- 6 cm /1.8 in/ ይደርሳል፡፡ በአንድ ቀን ውስጥ ከራሱ ክብደት በላይ የሆነ ምግብን ጥርግ ያረጋል፡፡ ስሙ ማን ነው ካስ እንብዛም እንግዳ አይደለም ያ የሚያውቁት አንበጣ ነው፡፡ አንድ ሺ ኪሎ ግራም የሚመዝኑ አንበጣዎች በቀን ውስጥ የ2500 ሰዎችን ምግብ አንክት ያረጋሉ ብንሎትስ? - አጃኢብ አንበለዎ!

# የመፀወተ አካበተ

«እናንተ ያመናችሁ ሆይ ካፈራችሁትና ከዚያም ለሃንተ ከምድር ካወጣንላችሁ ለግሱ»
አል በቀራ 267

ለአላህ ተብሎ የተሰጠ በፍፁም አይጐድልም፡፡ ለዘላለም የማይነጥፍ ምንዳን የጐናፀፋልና፡፡ ይህንንም አስመልክቶ አያሌ ቁርአናዊና የሐዲስ ማስረጃዎች ቢኖሩም በዋቢነት አንኳር አንኳሮቹን ለመቃኘት እንሞክራለን፡፡

ለአላህ ብለን ከምንለግሳቸው ዋንኛው ልጋሴ ቀጣይ፣ የማይቋረጥ በመባል ሲታወቅ ይህም ሞት እንኳ ቢቀድመን አይቀሬ አጅርን እያስመዘገበልን በዕለተ ትንሳኤ የመልካም ሚዛናችን እንዲደፋ አድርጐ የጀነት ባለሚሎች ለመሆን ያበቃናል፡፡ ለምሳሌ፡፡ መስጊድ መገንባት፣ ቁርአን ገዝቶ /አሳትሞ/ መቸር፣ ቤት ግንባታ ለድሆች ለሙታን ልጆች ማዘጋጀት፣ ትምህርት ቤት መስራት፣ እውቀትን ለሌሎች ማስተላለፍ፣ እውቀት እንዲተላለፍ መንስኤ መሆን፣ ህብረተሰቡ የማገለገልበት ድልድይ መገንባት ወዘተ...ከሞት በኋላም ሊጠቅሙ የሚችሉ የዘላለም አሴትን ያዘለ የተቀደሱ ተግባት ናቸው፡፡

ያለውን የሰጠ ንፉግ አይባልም እንዲሉ ኢስላማዊ የመስጠት ደንብ ከአቅም በላይ እንዳንቸገር አላደረገም፡፡ በጠራ ልቦና የተመፀወተ ትንሽም ይሁን ትልቅ ፋይዳው በጣም የላቀ ነው፡፡ በቡኻሪ በተዘገበው በአዲ ቢን ሃቲም በተነገረው ሀዲስ ውስጥ ነብያችን /ሰ.ዐ.ወ/ እንዲህ ብለው ነበር ...ሰዎች ሆይ እራሳችሁን ከገሃነም እሳት አድኑ፡፡ ሌላው ቀርቶ በግማሽ ተምር እንኳ ቢሆን፡፡ ይህ ከለላችሁ መልካም የወዳጅነት ንግግርን በመናገር እራሳችሁን አድኑ፡፡

መስጠት የእኩልነት ብስራት ነው፡፡ የአላህን መለኮታዋ ፍትህ ከቃኘን ሁሌም ሰጪ ነው፡፡ አየር ዝናቡን ብሎም ሲሳይ በረከቱን በነፃ የቸረ አምላክ ነውና

አላህ /ሱ.ወ/ የሚሰጠን ይወዳል፡፡ ስለምን ካሉ የርዕሱን ባህሪ ፈለግ ተከትለዋልና በመሆኑም ለመልካም ለተደላደለ ህይወት ያጫቸዋል፡፡

«የሰጠ ሰውማ፣ ጌታውን የፈራም በመልካሚቱ /እምነት/ ያረጋገጠ ለገሪቱ ስራ እናዘጋጀዋለን፡፡»
አል ለይል 5-6

በአንፃሩ የመስጠትን ባህሪ ጊዜ ቦታ ለደት የማይወስነው የህይወትና የሞት ዋስትና ነው፡፡ ከልብ ከመነጨ ስሜት ቸር መሆን የአላህን የጥበቃ ጥላ ያጐናፅፋል፡፡ በሁለቱም ዓለማት ከሚመጡ የፍርሃት ስሜቶች ነፃ ያደርጋል፡፡ ቁርአንን እነሆ

«እነዚያ ገንዘቦቻቸውን ብሌትና በቀን በድብቅም በግልፅም የሚሰግሱ ለነርሱ በጌታቸው ዘንድ ምንዳቸው አላቸው፡፡ በነርሱም ላይ ፍርሃት የለባቸውም እነርሱም አያዝኑም፡፡»

አል በቀራህ 2-74

የመስጠት ባህሪን ማጣደፍ የተወደደ ከመሆኑም ባሻገር ጠቀሜታው በጣሙን የላቀ ነው፡፡ ሞት ቀጠሮ ስለማያውቅ ዕድሉ ካመለጠ ለፀፀት ያድርጉ ደስታዎ ምንዳዎ የላቀ ይሆናልና

«አንዳችሁንም ሞት ሳይመጣውና ጌታዬ ሆይ እንድመፀውትና ከደጋጐቹ ሰዎች እንድሆን ወደ ጥቂት ጊዜ ብታቆየኝ ኖሮ እመኛለሁ ከማለቱ በፊት ከሰጠናችሁ ሲሳይ ለግሱ፡፡»

አል ሙናፊቁን 10

ሸይጧን በኛ ላይ ክተቱን ያወጀ ግልፅ ጠላታችን ነው፡፡ ሁሌም በመፈታተን መረቡ አጥምዶ በክስረት ታንቧ ሲያሳፍረን ይጥራል፡፡ ሸይጧን በፍፁማዊ የአላህ ቃል ኪዳን ላይ የጥራጣሬ መርዝን ችልሶ በነፍስያ ተባባሪነት መለኮታዊ እምነት /ተወኩልን/ በመቀነስ የምንዳችን ቀመር ሲያሽቆለቁል ለማየት ይጓጓል፡፡ ከዚህ በነቃ አዕምሮ እንጠነቀቀው ዘንድ አላህ እንዲህ ብሉ በቁርኣኑ አስጠንቅቆናል፡፡

«ሰይጣንም /እንዳትለግሱ/ ድህነትን ያስፈራራችኋል፡፡ በመጥፎ ያዛችኋል…»

አል በቀራህ 268

በተለያዩ ግዚያት፣ በተለያዩ አገሮችና አህጉራት ኢስላማዊ ተቋማትን መስጂዶችን ለመገንባት ተንቀሳቃሽ የሆኑት የማህበረሰቡ አባላት በግል በጋራ የመንቀሳቀሳቸው ሂደት ቋና የሚኖር ነው፡፡ ለዚህም ስተቀደሰ ተግባር አቅም በቻለው መጠን መሳተፍ ኢስላማዊ ፋና ከመሆኑም ባሻገር ከሞት በኋላም ላለው ህይወት የመሰረት ድንጋፍ መሆኑን ረሱል /ሰ.ዐ.ወ/ በዋስትና እንዲህ በማለት ያረጋግጡልናል…ለአላህ ብሉ መስጊድን የሚሰራ ማንኛውም ሰው፤ የወፍ ጉጆ ቢያክልም እንኳ አላህ ለርሱ ጀነት ውስጥ ቤት ይሰራለታል፡፡ አህመድ ዘግበውታል-አልባኒ ሶሂህ ብለውታል፡፡

ታዲያ ማንነው አቅሙ በፈቀደው መጠን ተጣጥሮ በገነት ውስጥ ቤት ማግኘትን የማይሻ ፍጡኑ ያመናችሁ፣…ይህ ክርክር ጥርጥር የሌለበት የሰናይ ብስራት ነው፡፡ ብዙ መወያየት ለሰይጣን የማታለል እስትንፋስ ቀዳዳን ይከፍታል፡፡ መርዳትን መስጠትን መመፅወትን ከውደይት በት ሲቀድሙ የሚገቡ መሆናቸውን የቁርኣንን ዋቢ እነሆ

«ከውደይታችሁ በፊት ምፅዋቶችን በማስቀደም /ድህነትን/ ፈራችሁን»

አል ሙጃደላህ 13

እንግዲህ ማን ነው በአላህና በመልዕክተኛው ያላመነ ማን ነው በላህ ቃል ኪዳን የተጠራጠረ ማንነው የጀነትን የይለፍ ወረቀት መያዝ የማይፈልግ ማን ነው በአላህ ጥበቃ ስር መሆን የማይፈልግ ማን ነው በመስጠቱ መንፈሱን እፎይ በማሰኘት ስነ ልቦናዊ ሃሴትን ማግኘት የማይሻ ...የለም ሁሉም ይህንን የሰናይ ጥሪን ይፈልጋል ብለ መወሰኑ የማያዳግት ቢሆንም ከላይ የተጠቀሰውን ለማግኘት ፈጣን እርምጃ /አቋም/ ያስፈልጋል እርምጃውም መስጠት ይባላል፡፡

«ለአላህና በመልዕክተኛው እመኑ /አላህ/ በርሱ ተተኪዎች ባደረጋችሁም ገንዘብ ለግለ አነዚያ ከናንተ ውስጥ ያመኑትን የለገሱት ለነርሱ ታላቅ ምንዳ አላቸው፡፡»

አል ሃዲድ 7

እህት ወንድሞች ሆይ ...አላህን አበድሩ ስለምን ካላችሁ እራሱው በቁርአኑ አበድሩኝ አለ የምህረት ውሳኔውን ለኛ እያከለ ሱቡሃነሏህ አላህ በድርን ሀሳ... እንዲያምር የኛ መጨረሻ ለጡ አይነጥፍም ሲሳዩ እስከመጨረሻ...መስጠት ነው የማግኘት መናገሻ...እራስን መፈወሻ...ከጀነት መድረሻ ልብ ያለው ልብ ይበል ወደ ቸርነት ይዘንበል የጀነትን ችግኝ በምድር ሳይ ይትከል...እህት ወንድሞች ሆይ ለአላህ አበድሩ...ማጣትን አትፍሩ ሰጥታችሁ ክበሩ...ቃለንም አክብሩ...

«የመፀወቱ ወንዶችና የመፀወቱ ሴቶች ለአላህም መልካም ቡድር ያበደሩ፤ ለነርሱ ይደራርብላቸዋል፤ ለነርሱም መልካም ምንዳ አላቸው፡፡»

አል ሃዲድ 18

የመፀወተ አካበተ ልብ ያለው ልብ ይበል

# የምእምናን ልቅሶ

መፅደቅን የሚሹ ሁሌም ያለቅሳሉ፡፡ ሀብታም፣ ደሃ፣ ነጭ፣ ጥቁር፣ ልዑል፣ ልዕልት፣ ባለስልጣናት እንኳ ሳይቀሩ፡፡ ሙስሊሞች በምስጢር ያዘሉት ሃይል ይህ ነው! በቀንም ይሁን በሌት መንታ እጆችን ወደ ፈጣሪ መዘርጋት መፀለይ መለመን ተግባራቸው ነው፡፡ ሙስሊሞች ካለባቸው ጫና አኳያ ታላቁ ሐይማኖት በፍጥነት የሚያድገው ሃይማኖት እየተባለ ኢስላም በመገናኛ ብዙሃን ባልተነገረ በጂኒየስ መዝገብም ባልተመዘገበ ነበር፡፡ ዱዓቸው ከቅኝ አገዛዝ አውጥቷቸው የቅኝ ገዢውንም ልጆች አሰላለማቸው ማን ቢሉኝ እነ የእንግሊዙ ካትስቲቨን /ዩሱፍ ኢስላም/ ታዋቂ ዘፋኝ የነበረውን ለምስክርነት ጠራለሁ አልበቃኝም ካለ ሌላ ብዙ ጨምራለሁ ግና አምድ ያጠባል፡፡ አልሃምዱሊላህ ከዚሁ ካሜሪካ የፈረንጅ አሊሞች /ምሁሮች/ ወጥተዋል፡፡ እነ ሐምዛ ዩሱፍን የመሣሠሉ፤ ታዲያ ማን አበቀላቸው መልሱ አጭር ነው የሙስሊሞች የሌት ተቀን ዱዓ! ፀሎት!

ሙስሊሞች የተዓምር ትርዒት የላቸውም፤ ለቅስቀሳ ፕሮጠጋንዳ የመገናኛ ብዙሃኑን እምብዛም አልጨበጡ የእምነት ሐብታም የቁስ ድሃ ናቸው፡፡ ዳሩ ከነቢዩ ሙሃመድና ደቀመዛሙሮቻቸው የእግር ኮቴ በታች መሬታቸውን በሚያልቅ በሚጠፋ ሀብት ሞላላቸው፡፡ ይህም ዱንያ አላቂና ጠፊ መሆኗን ያመለክታል፡፡ ነዳጁን ዘይቱን ማለቴ ነው፡፡

የስኬት ምንጫችን የምስጢር ጋሻችን ዱዓ ልቅሶአችን ነው፡፡ ስንፀልይ አሁኑኑ እንደምንሞት ስንሰራ ዘላለም እንደምንኖር አርገን እያሰብን ነው፡፡ መንፈስን ሥጋን አንነጣጥልም፡፡ የአንድ ሳንቲም ገፅታዎች ናቸውና! ሁሌም ዱዓ እናርግ ለሐጃችን! ከቻልንም እናንባ ፊታችንን ወደ አንድዬ መልሰን መሀሪ - ሩህሩህ - ቸር ነውና፡፡ እንግዲህ በዛሬው አምዳችን የምዕምናን እንባ እንቃኛለን ልቦናችን በአያሌው ይረጥብ ዘንድ! ታዲያ እንዴት ያለቅሱታል?

## 1. የአላህን ፍራቻ ለራስ ማስገንዘብ

«አላህን በመፍራት የሚደረግ ልቅሶ የጠቃሚ ዕውቀት ፍሬ ነው፡፡ አያለቅሱም በሽንጉበቶቻቸው/በአገጫቸው/ ላይ ይወድቃሉ ፍርሃትንም ይጨምርላቸዋል፡፡»

አል ኢስራዕ 109

አንቀፁ ልብን የሚነካ ገለፃ ነው፡፡ አማኒያን አላህን የሚፈሩ ሁሌም በአጅር ይክበሩ፡፡ ይህ የእያንዳንዱ ሙስሊም የእውቀትና የእምነት ደረጃ ቢሆን የላቀ ነው፡፡ ቁርኣንን ስናዳምጥ በፍራቻ በመተናነስ መሆን አለበት፡፡

## 2. ቁርኣን ሲቀራ ትርጉሙን ማሰላሰል

«አላህን ጥሩ ወይም አልረህማነን ጥሩ /ከሁለቱ/ ማንኛውንም ብትጠሩ /መልካም ነው/ ለርሱ መልካም ስሞች አሉትና! በላቸው በስግደትህም /ስታነብ/ አትጩህ በርሷ ድምፅህን ዝቅ አታድረግ በዚህም መካከል መንገድን ፈልግ፡፡»

አል ኢስራዕ 110

በተጨማሪም ይህ የእምነት ፍሬ የሆነው እንባ በነብዩ ዑመት ብቻ ያልተጀመረ መሆኑን አላህ /ሱ.ወ/ ሲያመላክተን እንዲህ ይላል፡፡

«እነዚህ /አስሩ/ እነዚያ አላህ በነርሱ ላይ የለገሣቸው፣ ከነብያትና ከአዳም ዘር ከኑህ ጋር /በመርከቢቱ ላይ/ ከጫናቸው /ዘሮች/ ከኢብራሒምና ከእስራኤል ዘሮች ከመራናቸውና ከመረጥናቸው የሆኑት የአረህማን አንቀጾች በነርሱ ላይ በተነበቡ ጊዜ ሰጋጆች አልቃሾች ሆነው ይወድቃሉ፡፡»

መርየም 58

ይህ ከደጋጉች የሚፈሰው የእምነት ምንጭ፣ ያለፈውንም ያሁኑንም የሚመጣውንም ኋጢዓታቸውን ከተማሩት ታላቁ ነብዩ ሙሃመድ /ሰ.ዓ.ወ/ ይፈልቅ እንደነበር ተዘግቧል፡፡ ታዲያ እኛስ ለአብነት ያህል በኢብን መስዑድ /ረ.ዓ/ የተነገረውን ሀዲስ እነሆ

«ነብዩ /ሰ.ዐ.ወ/ ቁርኣን ቅራ አሉኝ፣ የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! ቁርኣን ለርሶ ተገልጾ ሲያበቃ እኔ ላንብብን?» ነብዩም ሲመልሱ «ከሌላ ሰው ልሰማው እፈልጋለሁ» አሉ ሱረቱል ኒሳዕን እያነበብኩላቸው...

«ከህዝቦችም ሁሉ መስካሪን ባመጣን ግዜ፣ አንተን በነዚህ ላይ መስካሪ አድርገን በምናመጣህ ጊዜ /የከሃዲዎች ሁኔታ/ እንዴት ይሆን?»

አል ኒሳዕ 41

የሚለው አያ ጋር ስደርስ...ነብዩ «ለአሁኑ ይህ ይበቃል አሉ፡፡» ፊቱን ወደእርሳቸው ስመልስም እንባ አያመነጩ ነበር፡፡ ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል፡፡ እንግዲህ የከሃዲያን ሁናቴ እንዴት ይሆን ብሎ መጠየቅ ያቀረበው አላህ /ሱ.ወ/ የኛንስ ሁናቴ እንዴት ያደርገው ይሆን አምነናል ብለን መኩራራቱ፣ ለነገው ህይወት ምንም አለመሰነቁ አያስለቅስምን?

## 3. የማልቀስ ታሳቅነትንና ምንዳን ማወቅ፤ በተለይ ለብቻ ሲኮን

በአቡሁረይራ /ረ.ዓ/ በተነገረው፣ በቲርሙዚ በተዘገበውና፣ ሶሂህ በተባለው ሃዲስ ነብዩ /ሰ.ዓ.ወ/ እንዲህ ብለው ነበር፡፡ «አሳህን በመፍራት የሚያለቅስ ሰው ገሃነም አይገባም ወተት ወደ ግት ተመልሶ እስኪገባ ድረስ!...» ይህ ዘይቤአዊ አነጋገር ሲሆን ሊከሰት የሚችል መሆኑን በፅኑ ያመላክታል፡፡

በተጨማሪም በቡኻሪና በሙስሊም በተዘገበው ሃዲስ፤ ጥላ በማይኖርበት ዕለት የአሳህን ጥላ ከሚያስገኙት ሰባት ተግባራት አንድ ብቻውን ሲሆን አሳህን አስታውሶ እንባውን ያወረደ ነው፡፡ ታዲያ ብቻችንን ስንሆን አሳህን አስታውሰናል? ለምን እንደፈጠረን የወደፊት ዕጣ ፈንታችንን አስበናል? ወይስ ሲነጋ የምንናገረውን አሽሙር፣ የምናፌዘውን ፌዝ፣ የምንመቀኘውን ምቀኝነት፣ የምናጣሳውን ማጣሳት፣ የምንጐርረውን ጐራ፣ ነው የምናስበው አሳህ ይሁነን!

ከላይ በተጠቀሰው ሃዲስ መሠረት «አንድ ሰው ብቻውን ሲሆን» የሚለው ሀረግ ተነጥሎ መውጣቱ የሰው ልጅ ብቻውን በሚሆንበት ግዜ ልቦናው ይጠጥራል፤ ሀጢዓትን የመፈፀም ጠንካራና የጋለ ፍላጐት ሊኖረው ይችላልና ነው፡፡ ግን ይህን እርኩስ መንፈስ ታግሎ ጥራት ልዕልና ለተገባው አምላክ ለፀጋው አመስጋኝ በመሆን ከአይኖቹ እንባን ኮለል ሳደረገ፡፡ በመሃሪው የምህረት ዙፋን ላይ ተሠይሞ የመሃሪው ጥላ እንጂ ሌላ ጥላ በማይኖርበት ዕለት ከጥላው ስር መሆንን ይጐናፀፋል፡፡

በስደት የምንገኝ እህትና ወንድሞች ልብ ካለን ልብ እንበል፡፡ ለመሆኑ ሞትን አስበን እናውቃለን? የገርገራ /የጣር/ ህመም ሀያል መሆኑን አጢነናልን? አጋር - አጫዋች፣ ሀብት ንብረት፣ ገንዘብ ስልጣን በፍፁም ሊጠቅም የማይችልበትን አዛቡል ቀብርንስ? የናኪርና የሙንከር ጥያቄንስ? መን ረቡከ መባልንስ? እናት በልጇ የምትጨክንበት? የቂያማ ቀንንስ? ሲራጥንስ? ጀሃነምንስ? - አስበናልን? ታዲያ ምንድ ነው የምናስበው ስራ ብቻን ወሬ ማጣሳት ዶላሩን በወለድ ብድር ቤት መኪና መግዛቱን...እኮ አኬራስ መስገዱስ መቅራቱስ ኸይር መስራቱስ? ኧረ ኢባዳው ብዙ ነው አሳህ ይሁነን!

## 4. ስለ ሁናቴአችን ማሰብ፤ ከሰራነው ኃጢዓት ጋር እንዴት ብለን አሳህ ፊት እንቀርባለን በማለት!

ጥሩ ሰዎች የሰሩትን ኋጢዓት በማስታወስ፤ ከአይን የቀረበው አምላክ የሚቆጣቸው እየመሰላቸው ያነባሉ፡፡ ስለምን ቢሉ ኃጢዓት የሚሰሩና የማይሰሩ እኩል አይደሉምና ነው፡፡

> «እነዚያ ኃጢዓአቶችን የሰሩ ህይወታቸውም ሞታቸውም ትክክል ሲኾን፤ እንደ እነዚያ እንደአመኑትና መልካሞችን እንደሰሩት ልናደርጋቸው ይጠረጥራሉን /አይጠርጥሩ/ የሚፈርዱት ምነኛ ከፋ፡፡»
>
> አልጃሲያህ 21

ታዲያ ይህ ቁርኣን ተራራ ላይ ቢወርድ ኖሮ ይደረመስ ነበር፡፡ የሰው ልጅ ምንኛ አስቸጋሪ መሆኑን ልንረዳ እንችላለን፡፡ ቀልበ ደረቅ ከሚባሉት እንዳንመደብ ኃጢዓታችንን እናስታውስና እራሳችንን እራሳችን በመበደላችን ከአይኖቻችን ውኃ ይቅሰጥ ብረትን አላዩም በእሳት ሲቀልጥ እሣት ሲያስለቅሰው! ታዲያ ከዚያ የከፋው የጀሃነም እሳት ሲታሰብ አያስለቅስምን ጉዳናችን ወደ አረህማን ይቅና!

5. ለአላህ /ሱ.ወ/ ባላሟላናቸው ጉዳዮች መፀፀት

በሴት የሚፈስን የተፀፃች እንባን የኢስላም ሲቃውንት ሲገልፁት ጥምን አርኪ፣ ህመምን ፈዋሽ ይሉታል፡፡ ታዲያ በዱንያ አልታመምንምን? በነገር በምንትስ በቅብርጥስ፣ የትም ሳንደርስ ወደ አኼራ ብንመለስ፣ መዋላችን ለምን ነው በዋል ፈሰስ ዋ የድሜ ነገር ሲገሰግስ፣ መልክ ሲፈረስ፣ ቁንጅና ሲገሰስ፣ የሰው ልጅ በፌዝ በሣቅ ሲፈርስ አንተ በኒ አደም ሳቅ፣ ተፍለቅለቅ፣ ተሣለቅ በመለከል መውት ግን አይቀርም መታነቅ፡፡

> «ከዚህ ንግግር ትደነቃላችሁን? ትስቃላችሁንም? አታለቅሱምን? እናንተ ዘንጊዎች ናችሁ፡፡ ለአላህም ሰገደ ተገዙትም፡፡»
>
> አልነጅም 59-62

6. መጨረሻዬ ይበላሻል ብሎ በመስጋት ማልቀስ

አላህ /ሱ.ወ/ ኹስኑል ኻቲማችንን እንዲያሳምርልን ዘውትር ዱዓ ማድረግ አለብን እኛ እንደ ከሃዲያንና እንደምናፍቃን ልንሆን አይገባምና በኢብን ዑመር /ረ.ዓ/ በተነገረው ሃዲስ የአላህ መልዕክተኛ /ሰ.ዓ.ወ/

በአል ሒጅር መሬት /በሰሙድ ሰዎች/ በኩል ባለፉበት ወቅት እንዲህ አሉ፡፡ እነዚያ እራሳቸውን ያሳሳቱ ሰዎች ቤት እንዳትገቡ በነርሱ የደረሰ በናንተ እንዳይደርስ የምታለቅሱ ካልሆነ በስተቀር ከዚም የአላህ መልዕክተኛ እራሳቸውን ሸፍነው በፍጥነት ተራመዱ፡፡ ሸለቆውን እስኪያልፉ ድረስ ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል፡፡

7. ቀልብን የሚያረጥቡ ኢስላማዊ ንግግሮችንና ትምህርቶችን ማዳመጥ

እንግዲህ ማመካኘት ማሣበብ የኋላ ቀሮች ሆኗል፡፡ ኢስላማዊ ትምህርቶች በምድር አሜሪካ ሞልተዋል በካሴት፣ በቪዲዮ፣ በኢንተርኔት፣ በሬዲዮ በየመስጂዱ ይገኛሉ፡፡ አሜሪካ ተወልደው

ያደጉ ሰለምቴ ፈረንጆች ዓሊም የመሆን ደረጃ ደርሰው ቁርኣን፣ ሀዲስ፣ አረብኛን ለኛ መልሰው እያስተማሩ ነው፡፡ ታዲያ ምን እንጠብቃለን እንቀየር እንጂ መቼ ካሉ ዛሬ ፈጠን ፈጠን እንበል እነሆ አንድ ነብያዊ ሐዲስን ለመቋጫ

የተነገረው በኢረባድ ኢብን ሰዓሪያህ /ረ.ዓ./ ነው፡፡ እሱም ያለቅሱ ከነበሩት አንዱ ነው፡፡ እንዲህም አለ የአላህ መልዕክተኛ በጥልቅ የሚነካ ንግግር ሲያረጉ፣ አይኖቻችን በጣሙን ማንባት ይጀምሩና ልቦናችን ይቀልጥ ነበር፡፡ በቲርሙዚ፣ አቡዳውድና ኢብን ማጀህ የተዘገበ ሶሒህ ሀዲስ ነው፡፡

የነገን ብናውቅ ብዙ አልቅሰን ጥቂት በሣቅን ነበር ግና መሃሪው አምላክ ሁሌም ይምራል፡፡ በፀጋው በበረከቱ የምህረቱን ኩታ ያጐናፀፈን አሚን ጀነትን ዘላለም መዘውተሪያችን ያድርግልን ምን ይሳነዋል ሁን ብቻ ሳይነውና ከልቅሶው ቀን በፊት ምዕምናን ያለቅሳሉ፣ ልባዊ ሐሴትን በውን ይቀምሳሉ...

አላህ ሆይ! ውደደን ከምትወዳቸው አድርገን!

## በረካ እሙ አይመን

«ኡሙ አይመን፣ እናቴ ሆይ በአርግጥ በገነት ውስጥ ሳንቺ ቦታ አለሽ»
ነብዩ /ሰ.ዐ.ወ/

በረካ እንዴት በሽያጭ መካ እንደደረሰች አይታወቅም ስር መሰረቷ እናት አባቷ፣ አያት ቅድመ አያቶቿ አይታወቁም፣ የሚታወቀው እርሷን መሳይ አረቦች ወይም አረብ ያልሆኑ ህፃናትና ወጣቶች ለአስከፊው የባርነት ሽያጭ መቅረባቸው ነው፡፡ ዳሩ ግን በረካ ከዕድለኛዎቹ አንዷ ነበረች በቸሩ የአብልድ ሙጦሊብ ልጅ አብደላህ ጋር ነበረችና በረካም የነብዩ /ሰ.ዐ.ወ/ እናት አሚናህ አገልጋይና ጉዳያቸውን ፈፃሚ ነበረች፡፡ የአሚናህ ባለቤት አብደላህ በባታቸው ታዘው ለንግድ ሶሪያ መሄዳቸው ለአሚና አስደንጋጭ ዜና ነበር፡፡ ነፍሳቸውንም ሳቱ እንዲህ እያሉም ተንሰቅስቀው አለቀሱ፡፡ የሙስርነት ጠናዩ መስመሩ አልጠፋም እንዴት ውዱ ፍቅረኛዬ ጥሎኝ ይሔዳል ያለበረካ ማንም አፅናኝ አልነበራቸውም፡፡በዚያ ቀውጢ ወቅት ..ግና ሐዘኑ ለግዜው በደስታ ተተካ አሚናህ የሚያስደስት ህልም ያያሉ ደስታቸውንም ያጋሩት ለበረካ ነበር፡፡ ከሆዳቸው የሚፈነጠቀው ብርሃን የመካን ተራራሮች፣ አቀበቶች፣ ሸለቆዎች ሲያበራ ማየታቸው ነው ህልማቸው፡፡ በረካም ቀበል አድርጋ…

እመቤቴ የአርግዝና ስሜት ይሰማዎታልን ብላ ትጠየቃለች?

አዎ ቢሆንም ሴቶቹ ሲያረግዙ የሚሰማቸውን አይነት አለመቻቸት አይሰማኝም ይላሉ፡፡ አሚናህ በረካም ዘውትር ከእግርጌአቸው በመተኛት የናፍቆት የሐዘን የደስታቸው ተካፋይ ትሆናለች፡፡ ግን…የአብደሏህ ዜና የሚያስደስት አልነበረም፡፡ በንግዱ ጉዞ ሳይ ለህልፈት መብቃታቸው ይሰማል አሚናህ በድንጋጤ ነፍሳቸውን ይስታሉ በረካም ታለቅሣለች ትንሰቀሰቃለች በጋራ የሐዘን ተካፋይ ነበረችና

በዚህ የተደሰቱት ነብያችን እንዲህ በማለት አድናቆታቸውን ይገልፃሉ፡፡ …የተባረክሽ ነሽ በአርግጥ በገነት ውስጥ ቦታ አለሽ፡፡ ከዚያም በረካ ስትሔድ ዙሪያቸው ያሉትን ሰሃቦች ከተመለከቱ በኋላ…
ከናንተ መካከል ከጀነት ሰዎች አንዷ የሆነችውን ማግባት የሚፈልግ አለ ይላሉ ከወላጅ አባቱ ይልቅ ረሱል ጋር መኖር የመረጠው ዘይድ ኢብን አልሐሪዛህ የነበረውን ፀጥታ በቃለ ያደፈርስና የአላህ መልዕክተኛ ሆይ እኔ እሙ አይመንን ባገባት ደስ ይለኛል በአላህ ከማንኛውም ቁንጅናና ውበት ካደላት ሴት ትሻላለች ይላል ከበረካም ጋር ይጋባለ ልጅም ይወልዳሉ፡፡

ነብያችን /ሰ.ዐ.ወ/ መዲና ሲሰደዱ ቤታቸውን ለኡሙ አይመን አደራ ሰጥተው ነበር የኂዘት፡፡ ከነብዩ ሳስመለየት የዘላለም ቃል ኪዳን ያሳት እሙ አይመን አላስቻላትም፡፡ ብቻዋን ወደ መዲና አስችጋሪ ጉዞውን ታረጋለች በበረሃ በተራራሮቹ ሳይ፣ በለብላቢ ሙቀትና ሀራራ ሳይ በእግሯ ተጓዘች…ፊቷ በአቧራ ተሸፍኗል…እግሮቿ አብጠዋል ደክሟታል.. ግና የዘላለሙን እረፍት እንዳገኘች ከእንኳን ደህና መጣሽ ሰላምታ

በኋላ እንዲህ ብለው መስክረውላታል…የአይመን እናት …እናቴ ሆይ በአርግጥ በገነት ውስጥ ቦታ አለሽ በማለት ረሱል ይቀበሏታል፡፡

ነብዩ /ሰ.ዐ.ወ/ በሰላም ካረፉና ከዚህ አለም በሞት ከተለዩ በኋላ የበረካ አይኖት በእንባ ሲረጥቡ ይስተዋል ነበር ለምን እንደምታለቅስ ስትጠየቅም…

«በአላህ መልዕክተኛው እንደሚሞቱ አውቅ ነበር ግን ከላይ የመጣው ቁርኣን መቋረጠ ነው የሚያስለቅሰኝ ትላለች …በረካ /ረ.ዓ/…ኡሙ አይመን /ረ.ዓ/ ነብዩን ለማሣደግ በአላህ የተመረጠች ኢትዮጵያዊት…የአደራ እናት…ዘላለማዊ ትንግርት ነብዩ እናቴ ያሏት ነረበች፡፡» ኢትዮጵያዊት አልበረካ

እንግዲህ የመጨረሻው ነብይ እየመጣ ነው የነፍሰጡር እናቱን ችግር የሚጋራ፣ የሚኳድም በቀዬው ማንም አልነበረም ያለበረካ በስተቀር፡፡ ታላቁ ነብይ ሙሃመድ ኢብኑ አብደላህ ሲወለዱ ለመጀመሪያ ግዜ በበረካ ክንድ ላይ ነበር ያረፉት፡፡

እነሆ ያ ያፈቀረ ልቦና ቁርጠን ማየት ፈልጓል…ልክ ነብዩ /ሰ.ዐ.ወ/ ስድስት አመት ሲሞላቸው አሚናህ የትሪብ የሚባል ቦታ መሔድ ይፈልጋለ የባላቸውን መቃብር ለመጐብኘት በረካና አብድል ሙጠሊብ እንዲቀሩ ሃሣብ ያቀርባሉ…አሚናህ ግን ወይፍንክች እንዲስ እምቢኝ አሻፈረኝ ይሰና ለንግድ ይጓዝ ከነበረው የግመል ግትልትል ጋር ጉዞውን ይጀምሩታል በጠዋቱ በመዓልቱ ከበረካና ከሙሃመድ /ሰ.ዐ.ወ/ ጋር፡፡፡ ህፃኑ እንዳይጨነቅ ጉዞውን እንጂ የጉዞው ሁናቴ አልተነገረውም…ይህ ለአለም ህዝብ ወደር የሌለውን ተስፋ የጨበጠ ህፃን ይተኛ የነበረው በበረካ ክንድ አንገት ዙሪያ ላይ ነበር…ምነኛ የመረጠች አቢሲኒያዊት

እነሆ ምኞች ተሳካ አሚናህ የፍቅረኛቸውን መቃብር ጐበኙ በልቦናቸው ላይ ደስታን አናኙ የበረሃው ጉዞ ግን በጠና አሳመማቸው አል አብዋ የሚባል ቦታ ላይ ለጣርም ተታረቡ…ኑዛቤ ነበራቸው ለሐበሻዋ ወጣት …

በረካ ሆይ ከዚህ አለም ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ እንደምለይ ታውቆኛል ሙሃመድን አደራ ሆዱ ውስጥ እያለ አባቱን አጥቷል ይኸው አሁን ደግሞ አይኖቹ እያዩ እናቱን ሲያጣ ነው እናት ሁኚው በፍፁም አትለይው፡፡ ይላስ አሚና በጣር…አደራ …ከብረት የጠነከረ…ለሕማው ሁላ የተደሰኮረ …በበረካ ህልውና ላይ እንደቀሰበት የታሰረ አደራ አልአማና

ልቦናዬ በሃዘን ተነክቶ መንሰቅሰሱን ተያያዝኩት ትላለች በረካ…ህፃኑ ሙሃመድም ሁናቴውን አይቶ ሆድ ይብሰዋል፣ ማልቀስም ይጀምራል ተንደርድሮ በናቱ ጉያ ስር ይገባል…ነገሩ የቁርጥ ነበር አሚና የመጨረሻ ስቅታ አሰሙ…ለዘላለሙ ጉዞ ከዚህ አለም በሞት ተለዩ አሚና የሙሃመዱል አሚን እናት በረካ በእንባ ጠ ፍጠፍ ትታጠባለች በራሷው እጅ የአሚናህን መቃብር ትቆፍራለች…አደራ…የአሚናህን ግብአተ መሬት የመፈፀም አደራ

አደራ…የቲሙን ነብይ አያቱ ጋር የማድረስ አደራ…እነሆ ለአያቱ አስረክባ እንደ እናት ታሣድገው ዘንድ አብራው ትኖር ጀምራለች ግና የሀዘን ድር ማድራቱን ቀጥሏል…አያቱም ከሁለት አመት በኋላ…ሙሃመድን ጥለው ይሞታሉ…አሁንም አደራ… ዳግማዊ አደራ…ሳልስታዊ አደራ…የነብዩም መኖሪያ አጐታቸው አቡጧሊብ ጋር ይሆናል። ኸዲጃንም ሲያገቡ በረካ ነብዩን ተከትላ እቤታቸው መኖር ትጀምራለች። ለዚያም ነው ነብዩ ያ ኡማህ እናቴ እያለ የሚጠሯት።

አንድ ቀን ነብዩ /ሰ.ዐ.ወ/ እናቴ እያለ ይጣራሉ እኔ አሁን ባለትዳር ነኝ አንቺ እስከአሁን አላገባሽም ሰው መጥቶ ለጋብቻ ቢጠይቅ ምን ታስቢያለሽ ይላሉ…የአለሙ ብርሃን።

በፍፁም አልተዋትም እናት ልጇን ጥላ ትጠፋለች እንዴ ተላለች በረካ በእርግጠኝነት። ኸዲጃም ቀጠል አድርገው በረካን የስምኑ ገቡ በረካ ሆይ ለመሃመድ ስትይ ወጣት ነትሽን መስዋዕት አድርገሻል አሁን ደግሞ እርሱ ውለታሽን ሲከፍል ግዴታውን ሲወጣ ይሻል አባክሽን ለኔ ስትይ እድሜ ሳይቀድምሽ ለመግባት ተስማሚ ይላሉ አሚና

ማንን ነው ያሰቡልኝ? እመቤቴ በረካ ትጠይቃለች።

ዑበይድ ኢብን ዚያድ አጃችንን ሲጠይቅ* መጥቷል በአለሙ ብርሃን ባለቤት ስትለመን በረካ መስማማቷን ትገልፃለች። ጋብቻውም ይፈፀማል አይመን የሚባል ልጅ ትወልዳለች ትዳሯ ብዙም አልዘለቀም ባላ ከዚህ አለም በሞት ይለያል ዳግም ወደ ረሱል /ሰ.ዐ.ወ/ ቤት ትገባለች።

ዑሙ አይመን እስልምናናን ለማስፋፋት ሙስሊሞችን ከጥቃት ለማዳን በተለያዩ የትግል ጉራዎች ላይ አስፈላጊ መስዋዕትነት ከፍላለች መረጃ በማሰባሰቡ ረገድ ታላቅ ሚና ተጫውታለች ህይወቷንም ጭምር /ለአደጋ እየጣለች አንድ ቀን ቁረይሶች በሙስሊሞች ላይ ሲሰነዝሩ ያሴሩትን ጥቃት ለረሱል ትዘግብና የብዙ ሰው ህይወት ታተርፋለች።

---

* እጅ መጠየቅ በአረቡ አለም ቤትን ለማጨት የሚጠቀሙበት ያነጋገር ዘይቤ ነው።